#የመጀመርያ ዕትም

# ቀንዲል

Amharic Digital Magazine

ቅፅ-1 ቁጥር-1

EsQ Advertising



" ... እኛ ወጣቶች ከትንንሽ አስተሳሰቦች ነፃ በመውጣት ሀገራችንን ነፃ ማውጣት እንችላለን..."

**ሀና ሀይሉ**

## #አብርሆት
የአሸናፊነት ስነልቦና

## #ስነ-ፈለክ
ምስጢረ ከዋክብት

## #አጃኢብ
ኬንያዊው ጠበቃ ኢየሱስን በመግደል ወንጀል እስራኤልን ከሰሰ

ቀንዲል

Amharic Digital Magazine




## 3-4 #ሀገሬ
ሰፊ ይለበሳል ጠባብ ይቀደዳል
( ✍ በሀይሉ ወንድይፍራው )

## 5 #አብርሆት
የአሸናፊነት ስነልቦና
( ✍ ፍራኦል መስፍን )

## 6-9 #የአውደብሩሀን ገፆች
ቆይታ ከወጣት ሀና ሀይሉ ጋር

## 11 #አጃኢብ
ኬንያዊው ጠበቃ ኢየሱስን በመግደል ወንጀል እስራኤልን ከሰሰ
( ✍ ያብስራ ካሳ )

## 12 #ስነ-ፈለክ
ምስጢረ ከዋክብት
( ✍ ተባባሪ ፕ/ር አበበ ከበደ )

## 13-15 #ጤና ይስጥልኝ
የስንፈተወሲብ ምንነትና መፍትሄዎቹ
( ✍ ዶ/ር ፋሲካ አብርሀም )

## 17 #ቅምሻ
ዘሩ ብቅ አላለሞ ብለህ ውሀ ማጠጣቱን እንዳታቆም
( ✍ ኤርሚያስ ደጀኔ )

## 20 #ቴክኖሎጂ
የ 2018 ምርጥ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች
( ✍ ዞስ ካለስ )




# የአዘጋጇ መልዕክት

ሰላም!!

ባላችሁበት ሰላምታዬ ይድረሳችሁ!!

ይህ ከዚህ ቀጥሎ የምታነቡት የቀንዲል ዲጂታል መፅሔት የመጀመርያ ቅፅ ነው፡ ፡ ይህን ዲጂታል መፅሔት ተስፋ ለቆረጡት፡ መነቃቃት፡ ለደከሙት፡ ብርታት እንድትሰጥ፡ ብዙ ተጨንቀን እና ተጠብበን አዘጋጅተናታል፡፡ በይዘቱም አስተማሪ ፡ አዝናኝ እና አነቃቂ አምዶችን አካተን እንደ ምርጫቹ በዘርፍ ፡ በዘርፉ ሰድረንሎታል፡ ፡

የቀንዲል ትርጓሜ ፡- የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት እና ምርምር ማዕከል በአዲስ አበባ ዮኒቨርስቲ ባሳተመው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ላይ ቀንዲልን ሲገልፀው "ቀንዲል ማለት ከሻማ ፣ ከጧፍ ፡ የሚወጣው የመብራት ወጋገን፡ ቀንዲል ይባላል" ፡ ፡ እኛም ከዚህ ትርጓሜ በመነሳት ለመልካምነት ፣ ለቅንነት ፣ ለአንድነት ፣ ለሀገር ፍቅር ፣ ለዕውቀት ብርሀንነት መዳፍ ለመሆን ይህችን የዕውቀት ማዕድ ቀንዲል ብለን ሰይመናታል፡ ፡

በተጨማሪም ከተንኮል ፣ ከመጠላላት ፣ ከድህነት ጨለማ ሜዳ ላይ ቅንና ሀገር ወዳጅ ሆነን ትውልድ ልናነቃ ከቀንዲላችን ላይ የተስፋን እና የእውቀትን ብርሀን ይዘን ጽልመትን ድል ልንነሳ ይህው ጉዞ ጀምረናል፡ ፡

ቀንዲል ዲጂታል መፅሔት ለትርፍ ያልተቋቋመች መልካምነትን፡ ቅንነትን፡ በጎትን ማወጅ መርህ አድርጋ የተቋቋመች ከብሄር ፡ ከ ሀይማኖት፡ ከየትኛውም የፖለቲካ አመለካከት ነፃ የሆነ ሀሳብ የሚንሸራሸሩባት ፡ በሀገር ፍቅር በተሞሉ ወጣቶች ተዘጋጅታ ፡ ሀገራቸውን ለሚወዱ ኢትዮጵያውያን የቀረበች መፅሔት ነች!! ቀንዲል ዲጂታል መፅሔትን በወር አንድ ጊዜ በ ቴሌግራም እና በፌስቡክ ያገኟታል፡ ፡

✔አስተያየት በፍቅር ተቀብለን ደስ እያለን እናስተናግዳለን!!!

መልካም ንባብ ተመኙሁ!!

#ኤርሚያስ ደጀኔ

ዋና አዘጋጅ፡- ኤርሚያስ ደጀኔ
✆0912178520
E-mail ermiyasdejene@gmail.com
Telegram- @Jeremy00

አዘጋጅ፡- ሀና ሀይሉ
✆0935965345
Email- Hanahailu016@gmail.com
Telegram-@HanaHailu

አርታኢ፡- አወት ሀይለስላሴ
✆0920152581
E-mail- awoth12@gmail.com
Telegram-@Awicha12

የመፅሔት ዲዛይን እና Editing:-እስራኤል
✆0920019699
E-mail-- Esrumh1@gmail.com
Telegram-@EsruMH



በሀይሉ ወንድይፈራው
(መባ ጥቁር ሰው)

# ሰፊ ይለበሳል
## ጠባብ ይቀደዳል

*ከውቡ ምድርሽ ላይ ሰውነቴን ሰርቶ ከአላዋቂነትሽ*
*እውቀቴን ገንብቶ ያ ታላቅነትሽ በድንገት ሲጠፋ*
*በዝምታ ምታልፊ እፍኝ ባለተስፋ*
*በእውነት ተጽፈሽ የኖርሽ እስከዛሬ*
*የሰው ልጅ አሀዱ አንጂ ነሽ ሀገሬ፡*

ሀገር የሰው ልጅ መገኛው፣ መኖሪያው እና የማንነት መሰረቱ ከመሆን ባለፈ የህይወት ምህዳሩ ጅማሮ የአለምን ፊደል ማንበቢያ መጽሀፉ ጭምር ነው። የእውነታ ምልከታችን እና የመኖር ዘይቤያችን የምንቀስመው ከሀገራችን ምድር መሆኑ ሀቅ ነው ብዙዎች ስለ ሀገር ሲጠየቁ መግለጫ ያጣሉ ይህም የሆነው የአስተሳሰብ አድማሳችን መነሻ የሆነን ምድር መግለጫ ቃል በማጣታችን ነው።

ሀገር ከተራራው፣ ከወንዙ፣ ከእጽዋቱ፣ ከቋንቋው በተለየ መልኩ የሀሳብ መገለጫ ትርጓሜ መዝገበ ቀላትም ጭምር ነው ማለት ይቻላል ምክንያቱም የአንድ ሀገር ህዝቦች መለያ ሀሳብ እና ኑሮ ነው። ሀገራችን ኢትዮጲያ ካላት የተፈጥሮ ጸጋ እና ህዝቦቿ ከሰሯቸው ታሪኮች ባለፈ በህዝቦቿ ስብዕና የምትወደሰው እና የአለምን ቀልብ የገዛችው በህዝቦቿ የሀገር መግለጫ ሀሳብ ነው።

ኢትዮጲያ እጅግ አስደናቂ እና ልዩ ታሪክ ያላት ከአለም በፊት የሰለጠነች ሀገር ናት። ለብዙ አመታትም በሀይማኖት፣ በጥበብ፣ በመቻቻል፣ በጀግንነት፣ በስልጣኔ እና በአፈ-ታሪክ ብሂሎች ታጅባ የኖረች ንጉሳዊት ሀገር ምንጊዜም የአለም ህዝቦችን፣ ተመራማሪዎችን፣ እና መሪዎች ቀልብ ስታማልል የኖረች አሁንም የብዙዎችን ትኩረት እየሳበች የምትገኝ በሀሳብ እውደት የምትገለጽ በእምነት የተገመደች ታላቋ ኢትዮጲያ ናት። በምስራቅ አለም ውስጥ አንዲት ሚስጥራዊት፣ የጀግኖች ምድር፣ የመቻቻል፣ የክርስቲያን ደሴት የሆነች ሀገር አለች እየተባለ ገና ከመካከለኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በአውሮፓ ብሎም በመላው አለም ዝናዋ ይታወቅ ነበር። ቢዘህም ሁኔታ አያሌ አመታቶችን ከተቆጠሩም በኋላ ሀገራችን ጨለማው ተገፎ የሀገሪቱ ትክክለኛ ገጽታ እና ዕውነተኛ ታሪኳ ሲታይ በ አፈ ታሪክ ሲነገር ከነበረው የላቀ ሁኖ እናገኘዋለን።

በጣም ባልጎላችው የአፍሪካ አህጉር አለምን ተደብቀው የሚታዘቡ በሚመስሉት የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ተራሮች ውስጥ የምትገኘዋ ኢትዮጲያ ብዙ አመታትን ባስቆጠረው የነጻ መንግስትነት ታሪኳ ውስጥ አንድ ወጥ ልዩ ስልጣኔ ፈጥራለች። ሀገራችን ‹‹ ከ ጥቁር አፍሪካ ›› አገሮች የስልጣኔ ክልልም ሆነ በአህጉሩ ከሚገኙት የአረብ ሀገሮች የተለየች ናት። ከኢትዮጲያ ውጭ በዓለም በየትም አገር የማይገኘው የጽሁፍ ጥበቧ ለዚህ ምስክር ነው።

ሀገራችን ከዚህ የፁሁፍ ጥበቧ ባለፈ የምዕራባውያን የቅኝ ግዛት ፍላጎት በአፍሪካ ምድር ላይ በተዘራበት ጊዜ በህዝቦቿ ጀግንነት፣ መቻቻል፣ ፍቅር እና አንድነት ጠላትን ከማሳፈሯ ባለፈ ለመላው የጥቁር ህዝብ የነጻነት ብርሀን ያሳየች እና ያስተማረች የጀግኖች ምድር ናት።

ከዚህ የጥቁር ህዝብ የነጻነት ፋና ወጊ ከመሆኗ በላይ የታላላቅ ስልጣኔ እና ድርሳናት ባለቤት ነች ይህች የሀሳባችን ጥግ የሰውነታችን መለኪያ ሀገራችን። ታዲያ ይህች የአለም ስልጣኔ መሪ፣ የሰው ልጆች የመቻቻል ምድር፣ የጀግንነት አውድማ ዛሬ ቀና አርጓት ከነበረው ታሪኳ አንገቷን በድህነት፣ በኋላ ቀርነት፣ በጥላቻ ዝቅ አድርጋለች ይህም የሆነው የያኔውን ገናናነት አስጠብቀን ዘመናዊነትን በኛ ባህል መቃኘት አለመቻላችን እና የኛን እውነት በደንብ አለመረዳታችን ይመስለኛል። ከፍቅር ይልቅ ጥላቻን፣ ከቅንነት ክፋትን፣ ከአንድነት መራራቅን፣ ከመቻቻል መናናቅን፣ ከምክር መተቸትን፣ ከእርዳታ ስድብን፣ ከእውቀት ባርነትን ስለመረጥን እና ስለናፈቅን ዛሬ አለም ኋላ ቀር ብሎ ይጠራናል። በዚህ ሁሉ ግዜ ንጉስ ነውና አሁን አዲስ መንገድ ላይ ነን ይህ መንገድ እድል ነው በተለይ ለኛ ለወጣቶች ከሰፊው የአንድነት፣ የእውቀት፣ የመልካምነትና የሀገር ፍቅር ባህር ላይ እየጨለፍን ሀገራችን ወደ ገናናነቷ መመለስ የሁላችንም የቤት ስራ ነው።

ለዚህ ዕትም ፁሁፌ ‹‹ ሰፊ ይለበሳል ጠበባብ ይቀደዳል›› የምትለውን መልዕክት ለናንተ አደረስኩ። ወዳጄ በዚህ የቅጽበት ውጤት በሆነ አለም ቋሚ ሰው የለም በሂወትህ በእያንዳንዱ እርምጃ ስትኖር በተቻለህ መጠን ለሰዎች መልካም ሁን፣ ሆደ ሰፊ ሁን ሰፊ ስትሆን ሰፊ ሀሳብ አለህ፣ ሰፊ ስትሆን ሰፊ ሀገር አለህ፣ ሰፊ ስትሆን ሰፊ አለም አለህ። ልብ በል አንተ የሰፊው እና አዕምሮው የተራቀቀው የሰው ፍጥረት ነህ በእሳቤህ እና በኑሮህ በጠበብክ ቁጥር ትቀደዳለህ የተቀዳደ ነገር መጨረሻው ደሞ መጣል ነው።

ስለዚህ እንዳትጣል ሰፊ ሁን ወዳጄ ዛሬ እኛ ስለ ጎጥ እና ቀበሌ ስናስብ ከሰፊው ሰውነት ወደ ጠባቡ ቋንቋ ስንወርድ በቋንቋ ሳይሆን በደግነት፣ በፍቅር ያኖሩን እናቶች ዛሬም ድረስ የመከራ በትር እየገረፋቸው ነው፣ ዛሬም ድረስ አደን እንደወጣ እንሰሳ እንጨት እየለቀሙ ይመግቡናል በዛም መሀል ሰውነቱን የረሳ እህቶቻችንን ይደፍራል ይህ ሁሉ መከራ ብሄር የለውም፣ ይህ ሁሉ ችግር ቋንቋ የለውም፣ ይህ ሁሉ ችግር የኛ ነው የሰሜን፣ የደቡብ፣የምዕራብ፣የምስራቅ ለዛ ነው ችግራችንን ለመፍታት አንድ መሆን ያለብን፣ መዋደድ እና መከባበር ግድ ይለናል ስለዚህ ጠበህ አትቀደድ ይልቅ ሰፍተህ የናትህን ወገብ አቅና ምክንያቱም ሰፊነት ባህር መሆን ነው ባህር ደሞ ሁሉን ቻይ ነው።
ለዚህ ፅሑፍ መደምደሚያ ይሆነኝ የገጣሚ ህሊና ደሳለኝ የሰፍ ሀገር ይዘን ጠቦ መሞቶ ይብቃን ጀባ አልኩኝ።

### የሰፋ ሀገር ይዘን ጠቦ መሞት ይብቃን
(ገጣሚ ህሊና ደሳለኝ)

አይችለው የለ እንጂ የልባም ትከሻ፣
ከውርደቱ ደጃፍ ነውሩን ማምለጥ ሲሻ፣
ገርፎ ማሳመን ነው የፈሪ ሰው በትር የሸንታም ሰው ጋሻ።

እንመን ግድ የለም...

ፍትህ አይታለምም ሀቁን እየሸሹ፣
የጠፋው እንዲገኝ እስኪ መጀመርያ ይፈተሽ ፈታሹ።
አቀርቅራ ታዝግም ትጎናበስ እንጂ መሄድ እስኪያድላት፣
ሰብረህ ስታበቃ ምርኩዝ እንኪ ብለህ ደርሰህ አትደልላት።
በኔ ብቻ በሽታ ጥበት እየቀጣን፣
በእናታችን እርስት በአባታችን መሬት መደገፊያ እያጣን፣
ቁልቁል እያሰቡ ምንድነው ከፍታ፣
መብት እየነጠቁ ምንድነው ግዴታ?
እስከ መቼ ተረት ግዴለም ይነጋል፣
መንገድ እየቀሙ ምርኩዝ ምን ያደርጋል?
አንተ እንደው ልማድህ አለስልሶ መግደል አሳስቆ መግፋት፣
ካብኩ እያሉ ማቅለል ሳምኩ እያሉ መትፋት፣
የበደል ላይ ጀግና እሬሳ ላይ መዛት፣
መዋረድን ሸሽት የአሽቃባጭ አፍ መግዛት።
እየሸሹ ትግል እየሮጡ ዛቻ፣
በጉንዳን ልቦና የነብር ዘመቻ።
የበላ እያሰረ የቀማ ቢገፈው፣
የሳተ እያረመ ያጠፋ ቢገርፈው፣
ጀግና ልማዱ ነው ባርያ ሆኖ ታሽቶ ንጉስ ሆኖ መግዛት፣
እያነሰ ገዝፎ እየሞተ መብዛት።
ያ ሸንታም ላመሉ በሬሳ ይፎክራል፣
ከፈሪ ገዳይ ድል የጀግና ሞት ያምራል።

ይልቅ......

በእኔ ልቅደም ትርክት የዘር ደዌ አያጥቃን፣
ከጎጥ ቀንበር ፍቱን ጠቦ መሞት በቃን።
የጸደይ ወይን ሆኖ የሀቅ እንባ ቢጥም፣
በድሎ መጀገን ጀብድ ሆኖ ቢረግጥም፣
የትግላችን ልኩ ያሳር ደም ቢያስምጥም፣
በሰፋ ሀገር ጠበን ኢትዮጵያን አንሰጥም!!!



በ ፍራኦል መስፍን
( በመቀለ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ሌክቸረር እና የአዕምሮ ሐኪም )
firaolmesfin8@gmail.com

# የአሸናፊነት ስነልቦና

ሁሉም ሰው አሸናፊ መሆን ይፈልጋል። ለመሆኑ ተሸናፊ መሆን የሚፈልግ ይኖር ይሆን⁉ የሆነው ሆኖ አብዛኛው ሰው ተመሳሳይነት ባለው በተለመደ ህይወት ውስጥ ሲኖር፣ ጥቂቶች ብቻ ህልሞቻቸውን ሲኖሩ እናያለን። ... "እንደማንኛውም ሰው የተለመደ ኑሮ መኖር ምኑ ላይ ነው ክፋቱ⁉" .... የሚሉ ይኖራሉ። ይህ ፅሑፍ በዚ መደብ ውስጥ ላሉት ትርጉም የለውም። ይህ ፅሑፍ የተጻፈው ስኬታማ መሆን ለሚሹና ተመሳሳይ ህይወት ለሰለቻቸው ነው።

በመጀመርያ ደረጃ አሸናፊ ከመሆናችን በፊት መወሰን ይገባናል። በሚያሳዝን ሁኔታ አብዛኛው ሰው የተሻለ ለመሆን ቢፈልግም አይወስንም። ያው ... እንደሚኖረው ይኖራሉ። ህይወት እንደመራቻቸው ይመራሉ። በደመ ነፍስ ... በፍፁም እጃቸው ያለውን ነገር በተሻለ ነገር ለመለወጥ አያስቡም።

ይህ ነገር ብዙ ሰዎች ላይ እንደሚከሰት አምናለሁ። ሁላችንም ትልቅ ስኬት ላይ በመድረስ ውጤታማ የመሆን አቅምና ችሎታ እንዳለን የታወቀ ነው። መልካም ውጠትም በመጠባበቅ ህልማችንን ተግባራዊ ለማድረግ እንሞክራለን።

ቢሆንም ግን በመንገዳችን የሆነ ቦታ ላይ .... የሆነ ነገር ይበላሻል።ሞክረንም ሳይሳካ ይቀራል። መልካም መልካሙን እያሰብን ሞክረንም ሳናሳካልን እንቀራለን። እውነታው ይህ ነው :- ህልማችንጋ ለመድረስ ምን ያህል ሞከርን? ምን ያህልስ ቆራጦች ነበርን?

አብዛኞቹ ሰዎች ምናልባት ለቀናት ሞክረው ነበር ይሆናል ... ሌሎች ደግሞ ምናልባት ለሳምንታት ... አንዳንዶች ደግሞ ምናልባት ለ ዓመታት ሞክረው ነበር ይሆናል! ... ነገር ግን እንዴት አርገው ክህሎታቸውን ማሻሻል እንዳለባቸው በፍፁም አልተማሩም ። ማሸነፍ ቀላል ነገር አይደለም ።

ህልምን መኖር በጣም ፈታኝ ነው። ለዝህም ነው ጥቅቶች ብቻ የስኬትን ጫፍ የሚነኩት። ይህ ማለት ግን ለኔና ለናንተ ጨርሶ የማይቻል ነው ማለት አይደለም። በእውነቱ ከሆነ ማንኛውም ሰው አሸናፊ መሆን ይችላል። ትልቁ ጥያቄ ግን ... " እንዴት! ?" የሚለው ነው ።

ስለ አትሌት አስቡ

በኦሎምፒክ ውድድር ላይ የሚወዳደር አትልት አይታችሁ ታቃላችሁ? በማንኛውም የ ስፖርት አይነት ላይ የሚሳተፉትን ማለቴ ነው። እያንዳንዳቸው እጅግ በጣም ቆራጦችና መንፈሳቸው የተነቃቃ ነው ።

እነዚ አትሌቶች በውድድሩ ላይ የሚያሳዩትን ትዕይንት ለመከወን ጥቂት ደቂቃ ብቻ ቢፈጅባቸዉም እራሳቸዉን ሲያሰለጥኑ ለዓመታት ኖሯል። እሯጮች ከወጣትነታቸው ጀምሮ ስልጠና ላይ ቆይተዋል። ሁሉንም አይነት ተግዳሮት አልፈዋል። በስተመጨረሻም በጥቂት ደቂቃ ውስጥ በሚደረግ ትዕይንት በኦሎምፒክ ብቁ ሆነው በድል ያጠናቅቃሉ።

ታድያ እኚን ሰዎች እንዲታገሱና እንድያሸንፉ ያደረጋቸው ነገር ምንድነው?! ትልቅ ህልም አላቸው‼ ከዚ በተጨማሪ ለህልማቸው ለሞት ፍቃደኛ ናቸው።

አንተስ⁉ ... ህልምህ ምንድነው? ... ህልም አለህ?

ህልምህ በውስጥህ ያለውን የማሸነፍ አቅም ያነሳሳል ።

ህልምህ አቅም ፣ ጉልበት ይሰጥሃል ። በማለዳ እንድትነሳ ፣ አምሽተህ እንድተኛ ፣ ከሌሎች በተለየ መልኩ ጠንክረህ እንድትሰራ ውስጥህን ያነሳሳል ።

ህልም አለህ? ምናልባት ፕሮፌሽናል አትሌት የመሆን ህልም የለህም ይሆናል ። ነገር ግን ህልምህ ማንኛውም ልብህ ያረፈበት ነገር ሊሆን ይችላል ።

ምናልባት ውጤታማ ተማር ለመሆን ይሆናል ። ወይ ደግሞ አንቱ የተባለ ነጋዴ ። ወይ ደግሞ የቤተሰብህን ኑሮ ቀይረህ የነሱን ደስታ ማየት ።

ምንም ይሁን ምን ህልምህ ትልቅ መሆን አለበት ። ህልምህ ... ስለ ህልምህ ስታስብ እንኳን የሚያስደንቅህ መሆን አለበት ።

በህይወትህ ማከናወን የምትፈልገው ነገር ግልፅ ያልሆነ መሆን የለበትም ። አብዛኛውን ወጣት በህይወታቸው ምን ማከናወን እንደሚፈልጉ ስጠይቅ ... ሐብታም መሆን ደስተኛ መሆን እንደሚፈልጉ
ይነግሩኛል። እነዚ ህልም አይደሉም ። ግልፅ ያልሆኑ ሰፊ ምኞቶች ናቸው። የምትፈልገውን ነገር ይበልጥ በለየህ ቁጥር ፤ ለህልምህ የበለጠ አቅም ይሰጠዋል ።

ታድያ ምን ላርግ ?!

አሁኑኑ ትንሽ ወረቀት አንስተህ ህልሞችህን ፃፍ ።

ይሄን የማታረግ ከሆነ ህልሞችህ ላንተ ይሄን ያህል አስፈላጊ አይደሉም ማለት ነው። የምር ህልሞችህን እውን እንዲሆኑ የምትፈልግ ከሆነ አሁኑኑ ይህን አድረግ ። ህልምህን በወረቀት ላይ አስፍርና የበለጠ የሚዳሰሱ አድርጋቸው። በትንሽ ነገር ረክተህ እንደማትቀመጥና ህልሞችህን ለማሳካት ማድረግ የሚገባህን ሁሉ እንደምታረግ ለራስህ ንገረው ።

ስኬትን ተመኘሁ!

ቸር እንሰንብት!

*የዛሬው የአውደበሩሀን ገጽ እንግዳችን ወጣት ሀና ሀይሉ ትባላለች በተለያዩ የማበረሰብ ግልጋሎቶች ላይ ትሳተፋለች እንዲሁም የተለያዩ የወጣቶች ንቅናቄ ላይ የምትሰራ ወጣት ናት ሀና ሀይሉን በይበልጥ ለማስተዋወቅ እና ተሞክሮዎቿን ለአንባቢያን ልታካፍል ከዝግጅታችን ክፍል ጋር ቆይታ አድርጋለች እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡*

**ቀንዲል:-** በመጀመሪያ የዛሬው የቀንዲል መጽሄት የአውደ ብሩሀን ገጽ እንግዳችን በመሆንሽ በቀንዲል መጽሄት ስም ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

**ሃና**: እኔም ለምስጋና ዝቅ ብያለሁ

**ቀንዲል**: በቅድሚያ እስቲ ወደ ጥያቄዎቼ ከመግባቴ በፊት ሀና ሀይሉን ለአንባቢያን አስተዋውቂልን

ሀና:- ሀና ማለት አሁን ካለችበት ቦታ ተነስታ እንከኖቿን በማረም ክፍተቶቿን በመድፈን ግድፈቶቿን በማንፃት የራሷን ወደፊት መሆን የምታስባትን ጥሩ ንቁ እና ብቁ ማንነት ያላት ሴት  ለመሆን የምታልም ብሎም የምትተጋ ሴት ናት!
ከዚ ባሻገር የተወለድኩት አዲስ አበባ ነው። 22 ዓመቴ ነው። በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የ3ተኛ አመት የማርኬቲንግ ማኔጅመንት ተማሪ ነኝ  ።

**ቀንዲል:-** እሺ አመሰግናለሁ ሀና በቀጥታ ወደ ጥያቄዎቼ ልሂድና ብዙውን ግዜ ወጣትነት በተለያዩ ጊዜያት የተለያየ ትርጓሜ ይሰጠዋል  እስቲ ሀና ወጣት እንደመሆንሽ  ወጣትነትን እንዴት ትገልጭዋለሽ?

**ሀና:-** ወጣትነት ማለት በመንቃት እና በመብቃት መሀል ያለ ድልድይ ነው!
የመራወጥ የመሯሯጥ የመፍጋት የመለወጥ ንዳድ ይበልጥ የሚቀጣጠልበት እሳት ነው!
ወጣትነት ስንነቃ ከራስ በመጀመር ሌሎችን የምንረዳበት ስናንቀላፋ ደግሞ ለማንም ሳንሆን የምንባክንበት ጊዜ ነው!
ወጣትነት ሲገባን ታሪክ የምንሰራበት ሳይገባን ታሪክ የምናጠለሽበት ዘመን ነው!
ወጣትነት ኢያለንበት የማያሳስበን ሲያልፍ የሚያንገበግበን ትንሽ እድሜ ነው!
ስለዚህ በዚህ ጊዜ ሁሌም እንደማስበው መድረሻችንን በደንብ በማየት እና ግባችንን በማስቀመጥ እያንዳንዱን ሰዓት በአግባቡ አቅማችንን አሟጠን በመጠቀም የሚገባንን ምክንያታዊ ህይወት ልንኖር ይገባል!

**ቀንዲል**፡- ተስፋ ቆርጠሽ ታውቂያለሽ....?

**ሀና:-** የ17 ዓመት ልጅ እያለሁ ሰለሞን ሲሳይ የሚባል mentor(መምህር) ነበረኝ እና፡ብዙ ነገር ያስተምረኝ ነበር እንዴት ማደግ እና መለወጥ እንዳለብኝ!
ሰለግላዊ እና ሙያዊ፡እድገት(personal and professional Development) የሚያወራ



## "......በር ላይ የነበሩት ጥበቃዎች እያዩኝ መሬት ላይ ወድቄ አለቀስኩ! ምናለ በደንብ አዳምጦ አይሆንም እንኳን ቢለኝ....."

ጥሪ መፅሄት እንዳዘጋጅ ፈተና ሰጠኝ ሰርቼ ብጨርስ የምሸለመውም ሽልማት ትልቅ ነበር!
በራሴ እንድማር ስለሚፈልግ በራሴ መስራት ጀመርኩ በጣም ቆንጆ ስሌትና ስኬት የሚል በነፃ የሚታደል መፅሄት፡አዘጋጀሁ!
ብዙ ፈተና ነበረው በተለይ ስፖንሰር ለማግኘት አንድ ትልቅ ድርጅት  ጋር ለብዙ ጊዜ ተመላልሼ በመከራ አለቃውን ካገኘሁት በኋላ ላናግረው ቢሮ ስገባ ልወጣ ነው! እየወጣሁ ንገሪኝ አለኝ ስልክ እያወራ ነው እኔንም አውሪ ይለኝ ነበር በአንዱ ጆሮ የሚያዳምጠኝ ስለመሰለኝ አጠገቡ እየተከተልኩ አወራ ጀመር. ከዛ መኪናው ውስጥ ገብቶ መስኮቱን ዝቅ አረገና እሺ ሰምቼሻለሁ አለኝ ከዛ የሰጠሁትን ሳምፕል መፅሄት እና ቢዝነስ ካርዴን ወደ ኋላ፡መቀመጫ ወርውሮት መልስ ሳይሰጠኝ ሄደ በር ላይ የነበሩት ጥበቃዎች፡እያዩኝ መሬት ላይ ወድቄ አለቀስኩ! ምናለ በደንብ አዳምጦ አይሆንም እንኳን ቢለኝ ቀኑን ሙሉ ምግብ ፡ሳልበላ የጠበኩት፡በእግሬ እየተንከራተትኩ ብዙ ጊዜ የለፋሁ ለዚ ነበር! ከዛ ቀን ጀምሮ ህትመት ብቻ የቀረውን መፅሄት፡ያውም ትንሽ ስፖንሰር እያለው ተስፋ ቆርጬ እርግፍ አድርጌ ተውኩት ግን ብዙ ተማርኩ **ብዙ** ሰው አወኩበት! ሌላው ቢቀር ሰዎችን ማድመጥ እና የማይሆነውን ነገር አይሆንም ማለት ጥሩ መልስ እንደሆነ ገባኝ! መልሳቸውም እያወቁ አይሆንም ለማለት ቢሮ በቀጠሮ **የ**ሚያመላልሱን ብዙ ሰዎች አሉ!

ቀንዲል፡- እሺ ሀና የምትከተለው የህይወት ፍልስፍና ምንድነው ፍልስፍና ሰልሽ ያው በተለያየ አቅጣጫ ነገሮችን የምታይበትን ነው እንጂ የነ አርስቶትል ዘመንን አይደለም...

ሀና፡- .........ሳቅ.......
በርግጥ ፍልስፍና የለኝም ግን የምኖርበት ምክንያት ብዬ ማስበው
መንቃት እና ማንቃት
መብቃት እና ማብቃትን ነው!
መጀመሪያ ሌሎችን ለማንቃት ራስን፡ማንቃት እና ዙሪያችንን ማጤን ይገባል ስለዚህ ማንነቴ በጥሩ እሴቶች እና ስብዕና ለመገንባት እንዲሁም ከሰመመን ሙሉ በሙሉ ለመንቃት ያለኝን አቅም ና እድል፡ሁሉ እጠቀማለሁ! ከዛም ዙሪያዬ ያለን ሰው ማንቃት ስራዬ ይሆናል!
ብቁ ያልሆነ እረኛ ከብቶችን ማገድ እንደማይችል ሁሉ ብቁ ያልሆነ ሰውም ሌሎችን ማብቃት አይችልም ፡ራሴን ማብቃት ስራዬ ነው ያኔ ሌሎችን ማብቃት እችላለሁ ብዬ አምናለሁ።



**ቀንዲል**:- እንግዲህ በአሁን ሰዓት ላይ የተለያዩ የበጎ አድራጎት ስራዎልዎች ላይ እንዲሁም የማህበረሰብ አገልግሎት እየተሳተፍሽ ትገኛለሽ እስቲ ስለስራዎችሽ አጫውችን?

**ሀና**:- በጎ ነገር የምሰራው ለሰዎች ብቻ አይደለም ለሰው በጎ በማድረግ ውስጥ እኔ ያገኘኋቸው ብዙ በጎ ነገሮች አሉ! በገንዘብ ባይሆንም ከሰጠኸው በላይ ብዙ ታገኛለህ! በጎ ፍቃደኛ የሆንኩት ሌሎችን ለማስተማር እና ተፅኖም ለመፍጠር ጭምር ነው!
የ5ተኛ ክፍል ተማሪ ሳለሁ በመንበረ ህይወት መድህኒያለም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ክበባት ውስጥ ነው!
-አዲስ አበባ አቃቂ በሚገኘ የኢትዮጲያ ቤተሰብ መምሪያ. ..2002 ዓ.ም
(Right to play) በሚባል ቡድን(2001-2002)
-በዱከም ከተማ የህፃናት ፓርላማ..(2002ዓ.ም-2004ዓ.ም)
-በወጣቶች ማህበር (2005ዓ.ም)
-በፅናት የኪነጥበብ ቡድን(2005ዓ.ም -2006ዓ.ም)
*የመሰናዶ ትምህርት ቤት ሳለሁ በሰለሞን ሶልጃት የተመሰረተ (suneko Art for social Development) የሚባል ግብረ ሰናይ ድርጅት ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤ እና የግንኙነት አስተባባሪ በመሆን መሳተፍ ጀመርኩ!
ከዛ በተጨማሪ ያለ ክፍያ ብዙ ቦታዎች ላይ ሰርቻለሁ መፅሄት ላይ በሀሳብ ሽርሽር በሚል አምድ...ፊልም በቦታ መረጣ. ..አጫጭር ፊልሞች ላይ....ብቻ ባገኘሁት አጋጣሚ ሁሉ ለመስራት እሞክር ነበር! ዩኒቨርስቲ ከገባሁ በኋላ ይርጋለም ጠቅላላ ሆስፒታል ውስጥ በጎ ፍቃደኛ ሆኜ አገለግል ነበር
በመቀጠልም በጥሩ አጋጣሚ ጣሊታ የሚባለውን ግብረ ሰናይ ድርጅት የመጀመሪያ አመት የዩኒቨርስቲ ተማሪ ሳለሁ ተቀላቀልኩ። ብዙ የሰራ እና ብዙዎች ያላወቁት ቦታ ጣሊታ ነው!
አሁን በድርጅቱ ውስጥ የበጎ ፍቃደኛ አምባሳደር ነኝ!

**ቀንዲል**:- ሀና ከትምህርትሽ ጎን ለጎን ነው እንግዲህ እነዚህን ስራዎች እያከናወንሽ የምትገኝው ታዲያ እንዴት ነው ግዜሽን የምትጠቀሚው ያው ለሌለዎች ወጣቶች እና ለኛም ተሞክሮ በመሆኑ አካፍይን...?

**ሀና**:- ሁላችንም እኩል 24 ሰዓት አለን የምናሳካውን እና የምንሰራውን ነገር በትክክል የምናውቅ ከሆነ ለዛ የሚሆነውን ጊዜ በአግባቡ መጠቀም እንችላለን!
ለምሳሌ ጥዋት ከእንቅልፌ ስነሳ ቀኑን ሙሉ መስራት ያለብኝን ስራዎች ፅፌ ወይም አስተውዬ እወጣለሁ።
"መድረሻህን ካላወክ ሁሉም መንገድ ይወስድሀል " እንደሚባለው ሁሉም ነገር መድረሻን ወይም ግብን፡ከማስቀመጥ ይጀምራል
ይሄን መንገድ ሳልጠቀም ብዙ እቸገር ነበር....ሰኔ 1 ላይ ሆኜ ሰኔ 30 ማሳካት ያለብኝ ነገር ካለ መስራት ያለብኝን ለአራት ሳምንት ከዛም፡ ለ7 ቀን ከፍዬ ሁሉንም በየቀኑ መስራቴን አረጋግጣለሁ። ይሄ በጣም አድካሚ ቢሆንም ግን ውጤታማ ያደርጋል!

**ቀንዲል**:- እሺ እስቲ በመቀጠል ሀና ወደ ኬንያ ስለሄድሽበት አጋጣሚ እና በኬንያ ላጋጠሙሽ የተለያዩ ገጠመኞች ብሎም እይታዎች እናውራ?

**ሀና**:- በጣም የሚገርም ቆይታ ነበር እዛ የሄድኩት አይዜክ በሚባል አለም አቀፍ የወጣቶች ኔትዎርክ አማካኝነት ሲሆን ወደዛ ለመሄድ የሚያስፈልገኝን ወጪ በሙሉ የሸፈነው እግዜር ይስጠውና ደመቀ ጌታቸው፡የሚባል በውጪ ሀገር የሚኖር መልካም ሰው ነው..በርግጥ የምንተዋወቀው በፌስቡክ ነው ቢሆንም ሁሌ ጥረቴን ያየው ነበርና እኔ የተሻለ ቦታ እንድደርስ እኔንም ሆነ ሌሎችን ሰዎች፡ለማብቃት ሁሌም ዝግጁ ነበር! እዛ ስሄድ ያረፍኩት ማርታ የምትባል ጥሩ ሀበሻ ጋር ነው! ሰው ከጎረቤቱ ሲማር መልካም ነውና ከ100 በላይ ሀገሮች መሄድ ሲቻል ጎረቤታችንን መረጥኩ (ሀሀሀሀ.....ሳቅ)
በእውነት እነሱ በቴክኖሎጂ እና በእድገት ብዙ ሄደዋል....
ሊጠቅሙን የሚችሉ 3 ነገሮችን ለማንሳት እወዳለሁ...
1,የማንበብ ባህላቸው ከፍ ያለ ነው። ባስ ውስጥ ገበያ እና ጉልት ውስጥ ሳይቀር በእድሜ የገፉ እናቶች እንኳን መሬት ላይ ቁጭ ብለው ጋዜጣ ሲያነቡ አየሁ! እኛ እዚ ነገር ላይ መስራት አለብን
2, በሀይለ ስላሴ የተሰየመውን መንገድ አየሁ
ሚኒሊክ የሚባል ቦታ/መንገድ እንዳለም ሰምቻለሁ።
ጃንሆይም እስካሁን ልዩ ክብር አላቸው
በጆሞ ኬንያታ ጥያቄ መሰረት ለአንድ ሳምንት በሽግግር መንግስት ወቅት እንደመሯትም ይነገራል
በናሽናል ሙዚየማቸው ውስጥ ስገባ ምድራዊ ገነት ኢትዮጲያ የሚል ተፅፎ አንብቤያለሁ ታሪካዊ ንብረቶቻችን፡ተደርድረዋል
ኢትዮጲያ ሌሎች እንደሚያስቡት ብቻ ሳይሆን እኛም ገነት ውስጥ የምንኖር ያህል ሊሰማን ይገባል እና አንድነታችን ፍቅራችን ሰላማችን፡ላይ ማተኮር አለብን!
3, እኛ፡በስልጣኔ እንዳልቀደምን ....ፍፅም ያልተገዛች ሀገር እንዳልነበርን አሁን ግን በስልጣኔ፡ጎረቤቶቻችን፡ሳይቀሩ ብዙ ሄደዋል!
Wifi፣ውሀ፣መንገድ፣ መብራት ፣እኛ ጋር ዛሬም እንደችግር ይነሳል! እዛ የህዝብ ትራንስፖርት ላይ ሳይቀር wifi አለ !
በከተማው ውስጥ አርቴፊሻል ሀይቅ ሰርተው ሳይ እውነት ገርሞኛል ይሄንን ያህል አልጠበኩም፡ነበር!
በቀኝ መገዛታቸው ስማቸውን ቀይሮ ታሪካቸውን በርዞ ሀብታቸውን አሟጦ ቢጨርሰውም ለእድገታቸው የራሱ ድርሻ አለው!
እኛ ግን ሁሉም ነገር አለን! ከዚህ በላይ አንድ ሆነን ብንሰራ የምንደርስበትን ማሰብ ራሱ ይከብደኛል!
እግዚአብሄር ይመስገን ቢያንስ ያልተበረዘ ስምና ባህል አለን! በአያቶቼ፡ስም ውስጥ አንቶኒዮ እና ሮቤርቶ የለም!

**ቀንዲል**:- እሺ ባሁኑ ሰዓት ቅንዲል ኢትዮጲያ በሚባል የወጣቶች ንቅናቄ ውስጥ እየተሳተፍሽ ነው እስቲ ስለ ንቅናቄው እና ስለ አንቺ ድርሻ ሃሳቦችን አካፍይን?
**ሀና**:- እዚ ንቅናቄ ውስጥ ካሉ ወጣቶች አንዷ ባለራዕይ ነኝ! ብዙ ወጣቶች ባሉበት ቦታ የቻሉትን ያህል በቡድን፡ወይም በግል በኪነጥበብ በበጎ አድራጎት በተለያዩ የለውጥ ስራዎች ላይ ይሰራሉ!
እነዚህን ወጣቶች ወደ አንድ የጋራ መድረክ በማምጣት ቀጣዩን ትውልድ በመቀስቀስ በጋራ ለሀገራችን ትልቅ ለውጥ ለማምጣት የሚሰሩ ኢትዮጲያዊነትን መሰረት ያደረጉ የቅን ወጣቶች ስብስብ ነው!
**ቀንዲል**:- ከዚሁ ጋር ላያይዘው እና ወጣቶች ለሀገራቸው ስለሚያከናውኑት አበርክቶ ምን ሀሳ አለሽ?
**ሀና**:- እኛ ወጣቶች ራሳችንን ከትንንሽ አስተሳሰቦች ነፃ በማውጣት ሀገራችንን ነፃ ማውጣት እንችላለን። ጥሩ አስተሳሰብ የሌለው መሪ ጥሩ ተከታይ አይኖረውም እንደሚሉ ጥሩ መሪ ያልሆነ አባወራም ጥሩ ትዳር አይኖረውም ድንቅ ዜጋ የሌላትስ ሀገር እንዴት ታላቅ ትሆናለች!
መሬት ላራሹ. ...እድገት በህብረት እየተባለ ኢትዮጲያዊያን ወጣቶች መሀይምነትን ድል እንዳደረጉ ሀገራችንን እንዳራመዱት ሁሉ ኢትዮጲያም በዚህ ትውልድ ወደ ሌላኛው እድገት እንድትሄድ እኔ፡አንቺ እና አንተ በሁለት እግራችን ቆመን ሌሎችን ለማቆም እጃችንን መዘርጋት አለብን! አይደል?
**ቀንዲል**:- እውነት ነው ሀና ኢትዮጲያዊነትን እንዴት ትገልጪዋለሽ?
**ሀና**:- ድሮ ድሮ ከሀገሬ ውጪ ሀገር ከወገኔ ውጪ፡ሰው የሌለ፡ይመስል ኢትዮጲያነት የማንነቴ ልዕልና ነው እል ነበር! አሁን ግን ኢትዮጲያዊም ከመሆን በላይ ሰው መሆን ይልቃል ብዬ አምናለሁ!
ቢሆንም ከብዙ ሴቶች መሀል እናትን እንደምናስበልጥ. ..ከብዙ ወንዶች መሀል አባት ወንድምን ባልን እንደምናስበልጥ ሁሉ እኔም የምትቀርበኝን ኢትዮጲያ አስበልጣለሁ!
በመወለድ ሳይሆን በመላመድ እና በማዋደድ አምናለሁ! ከማታቁት አባት የምታቁት ጎረቤት አይበልጥም?
ኢትዮጲያ ስለምትቀርበኝ የለመድኳት ስለለመድኳት የወደድኳት ስለምወዳት ከፍታው የሚያስፈነጥዘኝ ዝቅታዋ የሚጠዘጥዘኝ ሀገሬ ናት! በጣም ከምወዳት ታናሽ እህቴ ጋር የቆዳ ቀለማችን ትንሽ ይለያያል ስለዚህ የትኛውም ኢትዮጲያዊ ወንድሜ እህቴ ወገኔ፡ነው! ኢትዮጲያዊነት ያለ እህቴ ያለቤተሰቦቼ፣ ያለ ታሪካችን ፣ያለ ጎረቤቶቼ ማሰብ ይከብደኛል! ኢትዮጲያዊነት በኢትዮጲያውያንን መኖር ውስጥ የሚኖር ህልውና ነው!
**ቀንዲል**:- ኢትዮጲያዊነት ሀሳብ ወይስ እውነት?
**ሀና**:- ኢትዮጲያዊነት እውነት ነው! እንኳን እየኖርክባት ርቀህ እንኳን የማትተወው እውነት!
እውነትማ ባትሆን ኖሮ ባሴሩባት ልክ ትወድቅ ነበር እኛም እንደዛው! መሰረቷ ጠንካራ እውነት ላይ ስለተገነባ ግርግዷዋ ይነቃነቃል እንጂ አትፈርስም!
ኢትዮጲያ ማለት የትላንትናዋ ታላቅ ሀገር ብቻም ሳትሆን አሁን የምንኖርበት እውነተኛ ሁኔታና ነገ የምናየውም እውነተኛ ተስፋችንም ጭምር ናት ኢትዮጲያዊነትም እንደዛው!

**ቀንዲል**:- እስቲ ከሀገራዊ ጥያቄዎቼ እንውጣ እና ሀና የተለያዩ ስራዎችን በምትሰሪበት ወቅት ያጋጠመሽ ገጠመኝ ካለ ብትነግሪኝ?
**ሀና**:- ትልቅ ህልም በማለም አምናለሁ! ትልቅ ነገር ስታልም ለሌሎች ቅዠት ይመስላል! አይሆንም ይሄ ይቅርብሽ. ...ይሄኛው መንገድ ይሻልሻል. ...ይሄን አትችይውም...ብዙ ግዜ ከልጅነቴ ጀምሮ ተብያለሁ! ቤተሰቦቻችን አስበውልን ሊሆን ይችላል...ነገር ግን አትችይም የሚለው ቃል አቅም እና ታሪክ እንዲሆነን፡ መድረስ ወደምንፈልግበት ቦታ ልንሮጥ ይገባል! ወደ መሰናዶ ትምህርት ቤት ስገባ የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪ እንድሆን ብዙ ጫና ይደረግብኝ ነበር ነገር ግን መሆን ያለብኝን አውቅ ስለነበር ለህልሜ ቅርብ የሆነውን መረጥኩ! የምንኖረው አንዴ ነው እሱንም ለኛ በሚመች እና በሚገባ መልኩ ልንኖር ይገባል!
ብዙ ስለፋ ብዙ ችግር ይገጥመኛል! ብዙ ያለቀስኩበት ቀን አለ ነገር ግን እነዛን ችግሮች መፍታትም የቻልኩት በራሴ ነበር! በተለይ የገጠመኝን ችግር(How to do....How to solve...How to correct.....) Google ላይ በመጠየቅ ወይም youtube ላይ አነቃቂ ወይም የግል ብልፅግና(personal Development) ቪዲዮዎችን በማየት ራሴን ከችግሮች፡ ነፃ በማድረግ ወደፊት እንድራመድ አግዞኛል! እድሜ ለጠሙኝ ችግሮች (ሳቅ...) ብዙ ሰዎችን እንዳማክር. ..ልምድ እንድጠይቅ፡....እንድማር ረዳኝ
**ቀንዲል**: እሺ ሴት እንደመሆንሽ መጠን የሴቶችን የመሪነት ብቃት እንዴት ታይዋለሽ አንቺስ መሪነትን በምን ትገልጭዋለሽ?
**ሀና**:- ሴት ልጅ ስትፈጠር ጀምሮ መሪ ነበረች! ቤቷን ልጆቿን ትመራለች! "ጀግኖችን ሁሉ ወልዳ የጀግነንት ሀሳብ በውስጣቸው ያኖረች ሴት ነች" ይላሉ አንድ መምህር
ሴትነት ተፈትነን ጥንካሬን የምንማርበት የተፈጥሮ ስጦታ ነው።
ሴት ልጅ መቻሏን ሁሉ ከተጠቀመች እንኳን የራሷን የሀገር ታሪክ ትቀይራለች! ምክንያቱም፡ጠንካራ እናት ያለው ልጅ ጠንካራ ከመሆን፡ውጪ አማራጭ የለውም!
**ቀንዲል**: እስቲ ስለ ግል ህይወትሽ እናውራ ሀና ምን ያዝናናታል ምንስ ያስከፋታል?
**ሀና**:- አዳዲስ ነገሮች ማድረግ ከአዲስ ሰዎች ጋር መተዋወቅ ...ብዙ ነገር ማወቅ መማር መሰልጠን ከሰዎች ጋር ኔትዎርክ ማድረግ. ....ያስደስታታል! ስልጠና ስብሰባ ውይይት በጣም መውደዷ ለየት ያደርጋታል! ያለ እንቅስቃሴዎች መዋል ያለ ስራ መቀመጥ ጥሩ ስሜት አይሰጠኝም! ብዙ ጊዜ እጅግ የምደሰተውም የማዝነውም በራሴ ነው። በተለይ እያወኩ ሳጠፋ በጣም እከፋለሁ..! ሰዎች ካስቀየሙኝ ኋላ ላይ የምናደደው እነሱ ባደረጉት ነገር ሳይሆን እኔ ለነሱ በሰጠሁት፡ምላሽ ነው። የሆነ ነገር ሞክሬ ካልተሳካ...አስቤ ከተውኩት...አዝናለሁ!

**ቀንዲል**፡- ሀና የመጀመሪያዋ የቀንዲል መጽሄት እንግዳ ሆነሽ ተሞክሮሽን ለሌሎች ወጣቶች ለማካፈል ፍቃደኛ ሆነሽ ሀሳብሽን ስላጋራሽን የቀንዲል ስም እያመሰገንኩ በመጨረሻ ማስተላለፍ የምትፈልጊው መልዕክት ካለ እድሉን ልስጥሽ?

**ሀና**:- "If you see it in your mind you can Hold it on your Hand" ይላል ቦብ ፕሮክተር በህሊናችን ያየነውን በእጃችን እንጨብጠዋለን...

ሲሳካለት ያሰበ ሲሳካለት ያያል...

በዚህ እድሜያችን የሚስበን ወይም የሚገፋን ህልማችን/እቅዳችን ሊሆን ይገባል ማህበራዊ ድረ ገፅ ላይ የምንፅፈውም የምናስተጋባውም ከህልማችን ጋር የሚሄድ መሆን አለበት! አለበለዚያ ሌሎች የፍላጎታቸው እና የህላማቸው ማስፈፀሚያ ያደርጉናል! የምንለብሰው የምናጌጠው የምናወራው በሙሉ ህልማችንን የሚያስተጋባልን ሊሆን ይገባል! በተጨማሪም ትላንት ስለሆነው ነገር ዛሬ ከመጮህ ዛሬ ለሚሆነው እና ነገ ስለሚቀጥለው ልናስብ ይገባል! ተስፋቸውን ዘወትር የሚያዩት ሰዎች ስለ ስራቸውና ስለራሳቸው ብሎም ስለለውጥ እና መለወጥ ያስባሉ ሀሳብ ያነሳሉ ሀሳብ ይጥላሉ! ስለዚህ ርዕሳችን ግለሰብ ሳይሆን ሀሳብ ኑሮአችንም የምናልመውን መምሰል አለበት! ለቀጣዩ ትውልድ ምን እናሳያቸዋለን አክሱም ላሊበላ የአባቶቻችን ነው....

እኛ ስናልፍ በዚህ ዘመን የሰሩት ተብሎ የሚጎበኝ ቦታ ምንድ ነው? ታርካችንስ እውነት ለማውራት ለመፃፍ ያጓጓል? ቀጣዩ ትውልድ እኛ በአባቶቻችን እንደኮራነው በኛ ደረታቸውን ይነፋሉ ወይስ አንገታቸውን ይደፋሉ?

ስለዚህ መንቃት አለብን

ብዙሀን ደማቸውን ላፈሰሱላት ሀገር ቢያንስ ላባችንን እናፍስስ ብዙሀን ህይወታቸውን ለሰጧት ሀገር ጊዜና ጉልበታችንን እንስጥ!

በመጨረሻም ትንሽ ጠይቄ ብዙ ለሚሰጠኝ ካሰብኩት በላይ ለሚያስብልኝ...ከፊቴ እየቀደመ ነገሮቼን ለሚያስተካክል ድንቅ ሰዎችን ለሰጠኝ እግዚአብሄር ምስጋና ይሁንልኝ!

ከታናሽ እህቴ ሄዋን ጀምሮ ወላጆቼ እንዲሁም ሌሎች ሲሳካልኝ ደስታ ስደክም ድጋፍ የሚሆኑኝ እንድነቃም እንድበቃም ያገዙኝ ብዙ ሰዎች አሉ እነሆ ለምስጋና ዝቅ አልኩ! እናንተም አመሰግናለሁ! ሰላም ለኢትዮጲያ

**ቀንዲል**:- እሺ እንግዲህ ሀና ሀይሉ የነበረን ቆይታ እጅግ አስተማሪ እና አዝናኝ ነበር በድጋሜ እንግዳችን በመሆንሽ አመሰግናለን አንባቢያንም ካንቺ የህይወት ተሞክሮዎች እና የጊዜ አጠቃቀም ብዙ ትምህርት እንደሚያገኙ ባለ ሙሉ ተስፋ ነን። አንቺም በቀጣይ ከዚህ በለይ ስኬቶችን በመብቃት እና በማብቃት እንደምታሳኪ ምንም ጥርጥር የለንም በሌላ ጊዜ በሰፊው ስለ ቅንዲል ኢትዮጵያ እና በሌሎች ስራዎችሽ እንምንገናኝ ተስፋ እናደርጋለን በቀንዲል ስም መልካም ጊዜ ተመኘሁ!

---------||----------

አለን የበጎ አድራጎት ማህበር

" we don't need a reason to help people!! "

አለን የበጎ አድራጎት ማህበር በተለያዩ ሚዲያዎች በሚሰሩ ጋዜጠኞች፡ የፊልም ተዋንያን፡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እና በተለያዩ የሙያ መስኮች ላይ በተሰማሩ ኢትዮጵያውያን የተመሰረተ የበጎ አድራጎት ማህበር ነው። ማህበሩ በዋናነት የካንሰር ህሙማንን በመደገፍ የሚያተኩር ሲሆን ሌሎች አቅመ ደካማ ህሙማንንም አለንላችሁ ይላል።

እርሶም ከእኛ ጋር " አለን!! " ይበሏቸው!!

ማህበሩን ለመደገፍ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000273591293 አልያም በአባልነት አብራችሁን ወገኖቻችንን አለን ለማለት፡-

✆0920017968 ይደውሉ

# መዝናኛ

«እን'ዳየሩ ጠባይ!!»
(✍ ናሁ አስተርአየ ጽጌ)

ከተራመድንበት : ከቆምንበት ምዕራፍ
ከፍተን ከዘጋነው : ካለፍንበት በራፍ
ከሄድንበት ሀገር
ካረፍንበት ማገር
ከተመረኮዝነው : ከታመንነው ነገር
ስሜት እየገፋን : ፊት ስንል የኋሊት
የናፈቅነውን ቀን : ያደርገዋል ሌሊት!!

አድማስ የሚከልል
አድማስ የሚያካልል
ሰማይን ምድርን: በተአምራት ገመድ : አስሮ ሚጠቀልል
ጠሐይን የሚያበርድ : በረድን የሚያግል
ከባብ ጋር ሚያዋድድ : ካንበሳ ሚያታግል
መንፈስ የሚያስጠምድ : በጥበብ መቃጥን
የመለኮትነት : ያምላክነት ውጥን
መግነጢሳዊ ኃይል : ሰው መሆን ያቀፈው
ባፍጢሙ ይደፋል : ስሜት ሲያናቅፈው!!

ቢደረጅ ትከሻው
ምን ደረቱ ቢያብጥም
ሺ ጊዜ ቢወፍር : ዕልፍ ቢፈረጥም
ከፍጥረት ስምሪት
አንድ የለም ለዘበት አደራ ተቀባይ
ሁሉ እየነፈሰ እንዳየሩ ጠባይ!!



በ ያብስራ ካሳ

# ኬንያዊው ጠበቃ ኢየሱስን በመግደል ወንጀል እስራኤልን ከሰሰ!

በአለማችን በየጊዜው የተለያዩ አስገራሚ የክስ አይነቶችን ሰምተን "አጃኢብ!" ብለን ይሆናል። ከወደ ከኬንያ የተሰማው የክስ ዜና ደሞ አነጋጋሪ ሆኗል ይለናል ኒውስ ኔት:: ነገሩ ወዲህ ነው ዶላ ኢንዲዲስ ይባላል ። ኬንያዊ ጠበቃ ነው። እነሆ ከ2000 አመታት በኋላ በክርስቶስ ላይ የተፈፀመውን ግፍ ችሎት ፊት ለፍርድ አቀርባለሁ ይላል ።

ጠበቃ ዶላ ለወንጀሉ እስራኤልን ቁጥር አንድ ተጠያቂ አድርጎ በተጨማሪም ሮማውያኑን ወይም የዛሬዋን ጣልያን ነገሥታት የነበሩትን ንጉሥ ሄሮድና ንጉሥ ታይቤርየሥን እንዲሁም በወቅቱ ክርስቶስን በሀሰት የወነጀሉ የዘመኑ የአይሁድ የሃይማኖት አባቶችን ክርስቶስ ላይ ለተፈፀመው ወንጀል ፍትህን አመጣለው በሚል አላማ በችሎት ፊት እገትራቸዋለሁ ይላል።

ከ2 ሺህ አመታት በኋላ ይህን ጉዳይ ፍርድ ቤት ለመውሰድ ጠበቃው ያሳዩት ወኔ የሚደነቅ መሆኑን የተናገረው ዘገባው ይሁን እንጂ ከህግ አኳያ ሊገጥማቸው የሚችለውን መሰናክል በዝርዝር አስነብቧል።

ዘገባው ከዛሬ 2ሺህ አመታት በፊት እስራኤልም ሆነ ጣልያን የሚባሉ ሀገሮች እንዳልነበሩ ጠቅሶ ንጉሥ ሄሮድ በወንጀሉ ላይ እጁ እንደሌለበት እና ከክርስቶስ ልደት በፊት በ4ኛው አመተ አለም ላይ ወይም ክርስቶስ ከመሰቀሉ ከ30 አመታት በፊት የሞተ ሰው እንደሆነ ይናገራል። ንጉሥ ታይቤሪየስም ቢሆን በክርስቶስ ስቅለት ላይ ቀጥተኛ ተጠያቂ ሊሆን የማይችል ሰው ሲሆን በመጽሀፍ ቅዱስ ላይ ስሙ አንድ ጊዜ ብቻ የሚጠቀስ ነው ይላል ዘገባው።

እነዚህን መሰል ነጥቦች የጠበቃውን ሙግት በፍርድ ቤት ተቀባይነት እንዳያገኝ ሊያደርግ እንደሚችል ሚናገረው ዘገባው አለም አቀፉ የፍትህ ፍርድ ቤት ወይም International Court of Justice (ICJ) እንኳን ለዚህ ጉዳይ ትኩረት አለመስጠቱ አያስገርምም በማለት ይናገራል። አለም አቀፉ የፍትህ ፍርድ ቤት በሀገራት መካከል ያሉ ውዝግቦችን እንጂ ይህን መሰሉን ጉዳይ እንደማይዳኝ ነውዘገባው የጠቀሰው። ይሁን እንጂ ኬንያዊው ጠበቃ ጉዳያቸውን ከኬንያ ፍርድ ቤት አልፈው ወደ አለም አቀፉ ፍርድ ቤት ቢወስዱትና በአንድ የሆነ ተአምር የሙግቱ አሸናፊ ቢሆኑስ ሲል ጥያቄ የሚያቀርበው ዘገባው ይህ የህግ ጉዳይ ሊኖረው የሚችለውን የህግ ክርክር በዝርዝር ይመለከታል።





በ ዶ/ር አበበ ከበደ
(Associate Professor of Physics, NCAT State University)
abekebede@gmail.com

# ምስጢረ ከዋክብት

የሰው ልጅ የሳይንስ እውቀት ኖረውም አልኖረውም ብዙ ጥያቄዎች ይጠይቃል። ተፈጥሮ ምንድነው? ከየት መጣ? ማን ፈጠረው ? ለሚሉት ጥያቄዎቹ በሚገነዘበው የተፈጥሮ ቅጥ (ፓተርን) እምነቱንና የሚከተለውን ህብረተሰባዊ ስርዓት ተከትሎ መልስ ይሰጣል ።ለምሳሌ የወቅቶች መቀያየር የጨረቃ መልክ መለዋወጥ የጸሃይ የጨረቃና የከዋክብት ብርሃን መለያየት የመሳሰሉት በተመልካች ላይ ከባድ የምርምር ጥያቄዎች ያስነሳሉ። በዚህ አምድ አንድ ሰው ሊጠይቀው የሚችለውን አንድ ጥያቄ አንስተን በጥንት የአባቶቻቸንን መልስ እናያለን። ጥያቄ፡ ጸሃይ ታበራለች ትሞቃለች ጨረቃና ከዋክብትም ያበራሉ ግን ብርሃናቸው ቀዝቃዛ ነው ይህ የሆነበት ምክንያቱ ምንድነው ? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ስማይን እንቃኝ።

ሰማይን እንቃኝ፡ ከዋክብትና ሕብረ ከዋክብት ከዋክብት እንዳቀማመጣቸው በሕብረ ከዋክብት ውስጥ ተመድበዋል። ፹፰ የታወቀ ሕብረ ከዋክብት አሉ። ከነዚህ ውስጥ ፲፪ቱ ጥንታዊነት አላቸው። አንድ ሕብረ ከዋክብት ዉስጡ ላለ አንድ ኮከብ አድራሻ ነው። ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ይህቺን ቅርጽ ይዞ ቢቆይም ዘመናዊው ሥነፈለክ በቢጫ የተከበውን ወስን ሰጥቶታል። ፐርሲየስ፤ አንድሮሜዳ (ብሩክታይት) እና ሲፍዩስ (የኢትዮጵያ ንጉስ) ያዋስኑታል። የጥንት የሰማይ ባላባቶች የግሪክ የግብጽ የባቢሎን የሲኖ የኑቢ የዓረብ ሰዎች ናቸው ይባላል።

ነገር ግን በብዛት ያልታወቁ ራሳቸውን የቻሉ ከማንም የማያንስ ከዋክብትን እና ሕብረ ከዋክብትን አቀማመጣቸውን እና አጓጓዛቸውን እያጠኑ ከብዙ ሺህ አመታት ጀምሮ ተፈጥሮን አሸንፈው እስከ አሁን ያሉ ነባር ጎሳዎች እንዳሉ ዘመናዊ ታሪክ ያስረዳል። በኢትዮጵያ ውስጥ የሥነ ፈላክ የተፈጥሮ እውቅት ካላቸው መካከል ኮንሶ፤ሙርሲ፤ቦረና፤በኤርትራ ደግሞ ትግረ የመሳሰሉት ጎሳዎች በባህላዊ ሥነፈለክ ጥናት ውስጥ በብዛት ይጠቀሳሉ።

የስው ዐይን ያለአጉሊ መነጽር 6000 የሚሆኑ ክዋክብትን ማየት ይችላል። በዘመናዊ አስራር የኮከብ ድምቀት ስድስት ደረጃ አለው ፩ኛ ደረጃ በጣም ድምቅ ያለ ሲሆን ፮ኛ ደረጃ የሆነው ደግሞ በጣም የደበዘዘ ሆኖ ጤነኛ ዓይን ከ፮ኛ ድረጃ በታች ማየት አይችልም።ሁለት ከዋክብት የደረጃ ልዩነታቸው ለምሳሌ ፭ ቢሆን አንዱ ኮኮበ ከሌላው ፻ ጊዜ ይደምቃል ወይም ይደበዝዛል ማለት ነው ።

ይህቺን ኖት ለማጠቃለል በጥንት ግዜ **ኢትዮጵያውያን የከዋክብትን ድምቀት መለያየት እንዴት አሰሉት** የሚለውን ጥያቄ እንመልሳለን። ይሄንን ጉዳይ ከመጻህፈ ሄኖክ ማግኘት ይቻላል ። ነገሩ እንደዚህ ነው ሄኖክ በኡራኤል አማክይነት ወደ ሰማይ ሄዶ ብዙ ነገሮችን ተምሯል ተገንዝቧል። እነዚህም ከዋክብት ጸሃይም ሆነ ጨረቃ አጓጓዛቸውን ሃይላቸውን ግንኙነታቸውን ወቅታዊ አወጣጣቸውን ህጋቸውን ስማቸውን ተገንዝቧል። በተጨማሪም የጸሃይን ጉዞ ከምስራቅ ወጥታ በምዕራብ እንደምትገባ በየወቅቱ የምታልፍባቸው ደጃፎችና ስማቸውን አውቋል። በተጨማሪም በነዚህ ደጃፎች ጨረቃም እንደምትጓዝ አውቋል። በተጨማሪም ጸሃይ ከሚነድ ነፋስ መሰራቷንና፤ የጸሃይ የከዋክብትና የጨረቃ ሃይል ልዩነትን በሒሳብ ተምሯል። ይህን ሒሳብ የኢትዮጵያን የከዋክብት ዕውን ድምቀት መለኪያ አድርጎ ማሰብ ይቻላል።

ሄኖክ የጸሃይ ተፈጥሮ ከእሳትና ከነፋስ ነው ይላል ። ጨረቃንና ከዋክብትን ከነፋስና ከውሃ አደረጋቸው እንዲህ አድርጎ ለይኩን ብሎ ከፈጠረው ከደገኛው ብርሃን ፈጠራቸው። የሃይላቸውን መጠን እንደሚከተለው አደላደላቸው ፤-የአንዲት የስንዴ ቅንጣት ያክል አምጥቶ ከሰባት ከፈለና ስድስቱን እጅ ለጸሓይ አደረገ። የቀረውን አንድ እጅ ከሰባት ከፍሎ ስድስቱን እጅ ለጨረቃ አንዱን እጅ ለከዋክብት አደረገ። በዚህ ምክንያት ሃይላቸው ወይም ድምቀታቸው ሊለያይ ቻለ።
በሒሳብ----- የጸሃይ ሃይል =6/7 የጨረቃ ሃይል =6/49የከዋክብት ሃይል=1/49
በዚህ ስሌት ጸሃይ ጨረቃን 7 ጊዜ በድምቀት ትበልጣታለች። ሁሉም ከዋክብት አንድ ጋር ሆነው ደግሞ ጸሃይ 52 ጊዜ በድምቀት ትበልጣቸዋለች ማለት ነው።

ይቀጥላል...



በ ዶ/ር ፋሲካ አብርሀም
faselove@gmail.com

# የስንፈተ ወሲብ

## ምንነትና መፍትሄዎቹ

በርካታ ባለትዳሮች በግልፅ ለመንገር ባይፈልጉም ከሁለቱ አንደኛው ከወሲብ የሚገኘውን ደስታ በመንፈጋቸው ሳቢያ ለዘመናት የገነቡትን ትዳር የጠዋት ጤዛ ሲያደርጉት አይተናል። ምንም እንኳን የስንፈተ ወሲብ ችግር ሳይንሳዊ ምክንያትና መፍትሄ ያለው ቢሆንም፣ ችግሩን በጋራ ለመፍታት የሚያስችል ግልፅነት ባለመኖሩ ትዳሮች ፈርሰዋል። ቤተሰብ ተበትኗል። ጥያቄው ያለው መፍትሄ ባለው ችግር ለምን ትዳሮች ይናጋሉ? ለምንስ ፍቅረኞች ወደ መለያየት ያመራሉ? የሚለው ላይ ነው።

### የስንፈተ ወሲብን ምንነትና በሁለቱም ፆታዎች በምን መልኩ እንደሚገለፅ በመጠኑ ብናየው?

ስንፈተ ወሲብ (Sexual Dysfunction) የምንለው በተለያዩ ምክንያቶች በሁለቱም ፆታዎች በኩል ወሲብ ለመፈፀም የሚያስችሉ ችግሮች ሲከሰቱ ማለት ነው። በሌላ አገላለፅ ደግሞ አግባባዊ (የሚያረካ) የወሲብ ግንኙነት አለመፈፀም አልያም በሚደረገው የወሲብ ግንኙነት አለመርካት (ጥሩ ውጤት አለማግኘት) ማለት ነው የስንፈተ ወሲብ ችግር የሚባለው።

**እንዴት ይገለፃል?** ለሚለው ለግብረ ስጋ ግንኙነት ስሜት ማጣትና ከግንኙነቱ እርካታ አለማግኘት በሁለቱም ፆታዎች ላይ የሚታይ ችግር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀሚያ አካላት አለመነሳሳትን በተመለከተ በአብዛኛው በወንዱ ላይ ይታያል። ፍላጎት ማጣት፣ ከግንኙነት በኋላ እርካታን አለማግኘት (የእርካታ መጨረሻ ላይ አለመድረስ) ብዙውን ጊዜ የሴቶች ችግር ነው ማለት ይቻላል።

### ለችግሩ መፈጠር መንስኤዎች ምንድናቸው?

የስንፈተ ወሲብን መንስኤ ስነ ልቦናዊና አካላዊ ብለን በሁለት ትላልቅ ጎራዎች ከፍለን መመልከት እንችላለን። አካላዊ ስንል ከግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀሚያ አካሎች ለውጥ፣ በደም ውስጥ ካሉ ንጥረ ነገሮች መዛባት፣ ከአዕምሮና ከህብለሰረሰር የሚነሱ ችግር ውስጥ ከመግባታቸው ጋር የሚያያዝ ነው። እንደዚሁም ከልብ የሚነሱ ደም ስሮች በአግባቡ ወደ ብልት ሄደው የደም ዝውውሩን ውጤታማ ማድረግ ባለመቻላቸውና ብልትን እንዲቆም የሚያደርጉ ነርቮች ባለመስራታቸው የስንፈተ ወሲብ ችግር ይመጣል። ሌላውና ከአካላዊ ምክንያት ጋር የሚያያዘው ስሜት ቀስቃሽ ንጥረ ነገሮች (ሆርሞኖች) በሚፈለገው መጠን በሰውነት ውስጥ አለመኖር፣ ስሜት ቀስቃሽ ንጥረ ነገሮች በሚፈለገው መጠን እንዳይሰሩ የሚያደርጉ ሌሎች የሆርሞን አይነቶች በሰውነት ውስጥ በብዛት ሲከሰቱ፣ በብልት ላይ የተለያዩ አደጋዎች ሲደርሱ፣ በብልት አካባቢ በሚሰሩ ቀዶ ህክምናዎች ምክንያት በብልት አካባቢ ያሉ ነርቮችና ደም ስሮች ሲጎዱ ለስንፈተ ወሲብ ችግር መጋለጥን ያመጣሉ።

በተጨማሪም ለሌሎች በሽታዎች መፈወሻ ተብለው የሚሰጡ ለምሳሌ ለደም ግፊት፣ ለጨጓራ፣ ለኮሌስትሮል፣ ለሽንት ማሸኛ፣ ለአዕምሮ ህመሞችና ለሌሎችም በሽታዎች የሚሰጡ መድኃኒቶች ችግሩን የማምጣት እድላቸው ሰፊ ነው። በአጠቃላይ 25 በመቶ የወንዶች ስንፈተ ወሲብ ለሌሎች በሽታዎች በሚሰጡ መድኃኒቶች የሚመጣ ነው።

ከስነ-ልቦና አንፃር ደግሞ ጭንቀት፣ ድብርት፣ ጫና፣ ውጥረትና ቀደም ሲል በነበረ የወሲብ ታሪክ ጥሩ ያልሆነ ክስተት ከነበረ ለምሳሌ በቅርብ ዘመዶችም ሆነ በሩቅ ሰዎች ተገዶ መደፈር ከነበረ ወሲብን መጥላት ይኖራል። በወሲብ መፈፀሚያ ቦታዎች አካባቢ ምቾት ማጣት፣ ከማይፈልጉት ሰው ጋር መኖር (ወሲብ መፈፀም) የወሲብ ስሜት አልባነትን ያመጣል። እንደዚሁም በአንድ ወቅት በሆነ ምክንያት ወሲብ ያለመፈፀም ችግር ገጥሞት ከነበረ ሁል ጊዜም ችግሩ አለብኝ ብሎ መጨነቅ ወደ ስንፈተ ወሲብ ችግር በቀጥታ የሚገፋ ሁኔታ ነው። ጠቅለል ባለ መልኩ መንስኤዎችን ስናየው አካላዊ ወይም ከበሽታ ጋር ተያይዞ የሚከሰተው ስንፈተ ወሲብ በአብዛኛው ከ40 ዓመት በላይ ባሉ ሰዎች ላይ የሚታይ ነው። በተለይም ከስነ ልቦና ጋር በተያያዘ ችግር ይበልጥ የሚጠቁት ወጣቶች ናቸው። ይሁን እንጂ ከስነ ልቦናዊ ምክንያቶች ጋር የተያያዘው የስንፈተ ወሲብ ችግር ከ10 እስከ 20 በመቶ የሚደርስ ነው። በሌላ በኩል ግን ከ40-80 በመቶ የሚሆነው የስንፈተ ወሲብ ችግር በቂ የሆነ አካላዊ ምክንያት ያለው ነው። ከላይ በመንስኤነት ከተገለፁ ጉዳዮች በተጨማሪ የሚገልፀው አብዝቶ አልኮል መጠጣት፣ ሲጋራ ማጨስ፣ ሐሺሽ እና ለመዝናኛነት ተብለው የሚወሰዱ መድኃኒቶች ችግሩን በማምጣት ረገድ የጎላ ሚና አላቸው።

### ስንፈተ ወሲብን በማምጣት ወይም በማባባስ በኩል አስተዋፅኦ ያላቸው የጤና ችግሮች

- ኢንፌክሽን
- የልብ ህመም
- የጉበት ህመም
- የኩላሊት ህመም
- የስኳር እና
- የደም ግፊት በሽታዎች እንደዚሁም
- የኮሌስትሮል ከፍ ማለት
- የጡንቻ መኮማተር (በተለይ በሴቷ)
- የደም ስር ችግሮች
- የነርቭ ህመም እና
- ሰውነትን የሚያንቀጠቅጥ ህመም (ፓርኪንሰንስ ዲዝዝ) ከላይ የገለፅኳቸው የጤና ችግሮች በአንድ በኩል ስንፈተ ወሲብን ያስከትላሉ። በሌላም በኩል ቀደም ሲል የተከሰተን ስንፈተ ወሲብ ያባብሳሉ።

### ስንፈተ ወሲብ መኖሩን ፍንጭ ከሚሰጡ ምልክቶች ዋና ዋና የሚባሉትን ብናያቸው?

- የወሲብ ፍላጎት ማጣት
- የወሲብ መፈፀሚያ አካላት ዝግጁ አለመሆን (አለመቆም)
- በተለይም ሴቶች ወንድንም ሆነ ወሲብን መጥላት
- ብልት ቶሎ ተልፈስፍሶ መውደቅ ወይም መርገብ
- ወሲብ በሚፈፀምበት ወቅት ህመም መኖር
- የሴት ብልት ጡንቻ መኮማተርና በሁለቱም ላይ ህመም መፍጠር
- ሴቶችን ለግንኙነት ዝግጁ የሚያደርግ ፈሳሽ በበቂ መጠን አለመኖር

### – እርካታ ላይ አለመድረስ

ፈጥኖ እርካታ ላይ መድረስ በሳይንስ እንዴት ነው የሚታየው? ፈጥኖ የዘር ፍሬን ማፍሰስ ችግር ያለባቸው በቁጥር ቀላል የማይባሉ ሰዎች ናቸው። ምክንያቱ ብዙ ነው። ዋናዋና የምንላቸው ምክንያቶች አንደኛው ለወሲብ ጉጉ ከመሆን የሚመነጭ ችኩልነት፣ ሁለተኛ ከአሁን አሁን የዘር ፍሬዬ ፈሰሰ ብሎ መጨነቅ፣ ሶስተኛ ራሴንም ሆነ ተቃራኒ ፆታዬን ማርካት አልችልም ብለው በተደጋጋሚ ስለሚያስቡ ስሜታቸውን ነፃ አድርገው ለመጋራት መቸገራቸው አራተኛው ከነርቭ ወይም ከብልት አፈጣጠር ጋር የተያያዘ ምክንያት ነው።

### የብልት ማነስ (መስፋት) ከስንፈተ ወሲብ ጋር ይገናኛል?

የብልት ጉዳይ ተፈጥሮአዊ ነው። ስንፈተ ወሲብ ደግሞ በቂ የሆነ አካላዊ አልያም ስነ ልቦናዊ ምክንያት ያለው የጤና ችግር ነው። ስለዚህ የብልት ማነስ ወይም መስፋት ከስንፈተ ወሲብ ጋር የሚያያዘው ነገር የለም።
አንድ ወንድ የዘር ፍሬ በማፍሰስ ብቻ ትክክለኛውን የወሲብ ድርጊት ፈፅሟል ማለት ይቻላል?
የዘር ፍሬ እኮ ምንም አይነት ግንኙነት ሳይደረግ የሚፈስበት ሁኔታም አለ። ስለዚህ የዘር ፍሬ መፍሰስ በራሱ ለውጤታማ የወሲብ ግንኙነት ማረጋገጫ አይሆንም። የአንድ ሰው ወሲባዊ ግንኙነት ጥሩ (ውጤታማ) ነው የሚባለው ወሲብ ከመፈፀሙ በፊት ያለውን ስኬታማ የፍቅር ጨዋታን ሁሉ የሚያካትት ነው። በተጨማሪም ጥሩ የወሲብ ግንኙነት ተደርጓል ለማለት ሁለቱም ፆታዎች የመጨረሻው እርካታ ላይ መድረሳቸው መረጋገጥ ይኖርበታል።

### ለስንፈተ ወሲብ ችግር ተጠቂ የሆነው ግለሰብ በተጣማሪው ላይ የሚፈጥረው አሉታዊ ተፅዕኖ

የሚያስከትለው ተፅዕኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። አንድ ግለሰብ ስንፈተ ወሲብ ውስጥ ማለት የእሱ ተጣማሪም የችግሩ ተጠቂ ናት ወይም ነው ማለት ነው። ይህ ሁኔታ ወደ ምን ያመራል ብንል ትዳርን ወደ ማፍረስና ወደ ብጥብጥ ነው የሚያመራው። ብጥብጡም ሆነ ትዳር መፍረስ የቤተሰብ መፍረስን ያከስትላል። በትዳር ውስጥ የተገኙ ልጆች ካሉም ይበተናሉ። በአካልና በስነ ልቦና ጤና የሚጎዱም ይሆናሉ። በተለይ ደግሞ ህፃናቱን የሚረዳቸው ከሌለ የማህበረሰቡ ችግር ሆኑ ማለት ነው። እንዲህ ያለው ሁኔታ በብዙ ሺህ ሰዎች ሲከሰት ደግሞ ችግሩ የግለሰቦች መሆኑ ቀርቶ የሀገር ይሆናል። የአሉታዊው ተፅዕኖ አንዱ ገፅታ ይሄው ነው። ሌላኛው ገፅታ ደግሞ የችግሩ ተጋላጭ በሆነው ግለሰብ ላይ የሚደርሰው ነው። የስንፈተ ወሲብ ችግር ያለበት ሰው በስነ ልቦና ህመም የተጎዳ ነው። ራሱን ይጥላል። የዝቅተኝነት ስሜትን ያሳድራል፤ ይህች ዓለም ለእኔ የተፈጠረች አይደለችም ወደሚል የተሳሳተ መደምደሚያ በመሄድ በራሱም ሆነ በአካባቢው ባሉ ሰዎች ላይ ጉዳት ለማድረስ እስከ መገፋፋት የሚሔድበት ሁኔታ ይኖራል። ሌላው ቢቀር ችግሩ እንዳለበት እንኳ አሜን ብሎ ለመቀበልና መፍትሄውን ባሉት አማራጮች ሁሉ ለመፍታት ፈቃደኝነትን ሊያጣ ይችላል።

ይህ ደግሞ ችግሩ አለብህ ብለው ሊነግሩት ከሚፈልጉት ሰዎች ጋር ሁሉ ፀብ የሚጭር ይሆናል። በአጠቃላይ ችግሩ ያለበት ሰው ከህይወት ጣእምን ያጣ ስለሚመስለው ሁልጊዜ ደስተኛ አይሆንም። በድብርትና በጭንቀት የተዋጠ የመሆን እድሉ ሰፊ ይሆናል።

### ችግሩ መኖር አለመኖሩን ለመለየት የሚያስችሉ ምርመራዎችስ?

ስነ ልቦናዊ ችግር ያለባቸውን ከዕድሜያቸውና ከሚሰጡን ታሪክ ተነስተን ማረጋገጥ እንችላለን። የችግሩ መንስኤ ከስነ ልቦና ውጪ አካላዊ ነው ብለን ካሰብን የተለያዩ ምርመራዎችን እናደርጋለን። ለምሳሌ ችግሩን ያመጣው በሽታ ነው ብለን ካሰብን በሚጠረጠሩ በሽታዎች ዙሪያ የላብራቶሪ ምርመራዎችን እናደርጋለን። የሆርሞን እጥረት (መዛባትን) ለማረጋገጥም የተለያዩ ምርመራዎች ይደረጋሉ።

እንደዚሁም በአካላዊ ምርመራ ችግሩ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ጥረት እናደርጋለን። በአጠቃላይ የስነፈተ ወሲብ ችግር መኖር አለመኖሩን የሚያረጋግጡ ምርመራዎች በሀገራችን በበቂ ሁኔታ ይሰራሉ። ውጤታማም ናቸው።

### ህክምናውስ?

የችግሩ መንስኤ በእርግጠኝነት ስነ ልቦናዊ መሆኑ ከተረጋገጠ ስነ ልቦናዊ ችግሩን መፍታት ላይ እናተኩራለን። ለምሳሌ ፈጥኜ እርካታ ጥግ ላይ እደርሳለሁ የሚል ከሆነ የዘር ፍሬውን ማዘግየት የሚችልበትን ዘዴዎች በማማከርና በማሰልጠን የማረጋጋት ስራዎችን እንሰራለን። ስነ ልቦናው ችግሩ የገዘፈና ስር የሰደደ ከሆነ ለተጨማሪ የማማከር ስራ ወደ ስነ ልቦና ሙያተኞች እንልከዋለን። በሌላ በኩል በሌሎች በሽታዎች ተብለው ከሚወሰዱ መድኃኒቶች ጋር በተያያዘ ችግሩ የመጣና የሚወስዱትን መድኃኒቶች ማቆም የሚቻል ከሆነ መድኃኒቶችን ከመውሰድ እንዲታቀብ ይመከራል። ነገር ግን የሚወስዷቸው መድኃኒቶች ማቆም የማይቻላቸው ከሆነ ከተቻለ መድኃኒቶች የሚቀየሩበትን ሁኔታ እንፈልጋለን። ካልተቻለ ግን ከገጠመው ስንፈተ ወሲብ ጋር ተስማምቶ የሚኖርበትን ሁኔታ እንዲያመቻች ተገቢውን ምክር እንዲያገኝ ይደረጋል። በተጨማሪም የስንፈተ ወሲብ ችግርን የሚያስተካክሉ በሀገራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ የመድኃኒት ገበያ በርካታ መድኃኒቶች አሉ። ነገር ግን እነዚህ መድኃኒቶችን መውሰድ ያለባቸው በዘፈቀደ ሳይሆን በሐኪሞም ትዕዛዝ መሆን ይኖርበታል።

ከሌሎች አማራጭ ህክምናዎች ደግሞ የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡
– የሆርሞን እጥረት ላለባቸው ሰዎች የሆርሞን መተኪያ ህክምና መስጠት
– በብልት ላይ በመግጠም ብልት እንዲቆም በማድረግ ወዲያው የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም የሚያስችል (vaccum device)
– ግለሰቡ በግብረ ስጋ ግንኙነት በተዘጋጀበት ወቅት ብልት ላይ የሚወጉ መድኃኒቶች አሉ
– በሽንት ቧንቧ ወደ ውስጥ የሚከተቱ መድኃኒቶችን መስጠት
– በቀዶ ህክምና የተፈጠረውን ችግር ማስተካከል
– ደም ስሮችን በቀዶ ህክምና ማስተካከል

ከአማራጭ ህክምናዎች የበለጠ ውጤታማው የትኛው ነው?
ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ከሆነ በአፍ የሚወሰዱ መድኃኒቶች የስኳርና ሌሎች የጤና ችግር በሌለባቸው ሰዎች ላይ ከ70 እስከ 90 በመቶ ውጤታማ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የስኳር በሽታ ባለባቸው ሰዎች ደግሞ መድኃኒቶቹ ከ50 እስከ 60 በመቶ ውጤት ይገኝባቸዋል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ከሙያው ጋር ቅርበት የሌላቸው ሰዎች ለስንፈተ ወሲብ ችግር መድኃኒት ሲያዝዙ ይታያል፡፡ አልፈው ተርፈውም የሆርሞን ህክምና ሲሰጡ ይስተዋላል፡፡ የሆርሞን ህክምናን ለመስጠት መታየት ያለባቸው ነገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ ካንሰር ላለበት ሰው የሆርሞን ህክምና ቢሰጠው ካንሰሩን በከፍተኛ ሁኔታ ያባብሰዋል፡፡ ስለዚህ ለስንፈተ ወሲብ የሚሰጠው ህክምና ሌላ ችግር እንዳያስከትል በጥንቃቄና ታስቦበት ሊሰራ የሚገባው ህክምና ነው፡፡

በፍቅርም ሆነ በትዳር ውስጥ ያሉ ጥንዶች መገንዘብ በሚገባቸው ለግንኙነታቸው መነሻም ሆነ መድረሻ አልያም ብቸኛው ጣዕም ሰጭ ወሲብ መፈፀም ብቻ ነው ብለው ድምዳሜ ላይ መድረስ የለባቸውም፡፡ ከወሲብ ይልቅ በቅድመ ወሲብ ወቅት የሚፈፀመው የፍቅር ጨዋታዎች የበለጠ ጣዕም ሰጭና ጠቃሚ መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ስለ ፆታዊ ግንኙነት የሚኖራቸውን እውቀት በእየዕለቱ ማሳደግን መዘንጋት የለባቸውም፡፡ ምክንያቱም ይህ የፍቅር ጨዋታ ጭንቀትንም ሆነ ወሲብ በአግባቡ የመፈፀም ብቃት የለኝም የሚለውን የፍርሃት ስሜትን የማጥፋት እድሉ ከፍተኛ ነው፡፡

በተፈጠረው ችግር ዙሪያ በግልፅ መነጋገርና አንዱ አንዱን ለመርዳት እንዲሁም በጋራ መፍትሄውን ለማፈላለግ ፈቃደኝነት ማሳየት ይኖርባቸዋል፡፡ ችግሩ በሴቷም ሆነ በወንዱ ይድረስ ብጥብጥ ከመፍጠር ይልቅ እንዲህ አይነት ችግር ይፈጠራል፣ ምንም ማለት አይደለም፣

ያለወሲብ መኖር እንችላለን ወዘተ... የሚሉ የማበረታቻ ቃሎችን ለተቃራኒ ፆታ መስጠት ያስፈልጋሉ፡፡ በሁለቱ መረዳዳት ችግሩ የማይፈታ ከሆነ ወደ ባለሙያ ሄደው በችግሩ ዙሪያ በግልፅ መነጋገርና መፍትሄ መፈለግ ይኖርባቸዋል፡፡
ጭንቀትን፣ ድብርትን፣ ውጥረትንና መሰል ስነ ልቦናዊ ችግሮችን ለማስወገድ ጥረት ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡ አልኮል ከመጠጣት፣ ሲጋራና ሀሽሽን ከማጨስ መታቀብ እንደዚሁም የውስጥ ጤና ችግሮች ካሉ በወቅቱ መታከምም ተገቢ ሆናል፡፡ በአጠቃላይ የስንፈተ ወሲብ ችግሩ ከመድኃኒት ጀምሮ እስከ ቀዶ ህክምና የሚዘልቅ የህክምና መፍትሄ ያለው በመሆኑ ጥንዶች ትዳራቸውም ሆነ የፍቅር ግንኙነታቸውን ቀውስ ውስጥ ከመክተት በፊት ተረጋግተው ለመፍትሄው በጋራ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ በትዕግስት ጥረት ማድረግም አለባቸው፡፡

ምንጭ-ስለ ወንዶችም ሆነ ሴቶች ስንፈተ ወሲብ ከባለሙያ ጋር የተደረገ ቃለምልልስ
March 13, 2015 Posted by: ዘሐበሻ

ቅንዲል
ON FACEBOOK
ON TELEGRAM
ያግኙን
0912178520
0920019699

# 250 ሺህ በላይ ሰዎችን ይድረሱ!

ምርትና አገልግሎትዎን በ ቀንዲል
ዲጂታል መፅሔት በልዩ አቀራረብ
ያስተዋውቁ ከማስታወቂያ የሚገኘው ገቢ በግማሽ ለበጎ
አድራጎት ስራ የሚውል ምርት እና አገልግሎቶን
እያስተዋወቁ የበጎ አድራጎት ስራ ይስሩ!!

## ለበለጠ መረጃ

(+251) 0912178520
(+251) 0920019699

**ይደውሉ!**



በ ኤርምያስ ደጀኔ
ermiyasdejene@gmail.com

# ዘሩ ብቅ አላለም ብለህ ውሃ ማጠጣቱን አታቁም!!!

አንዳንዴ ለፍተን ለፍተን ምንም ነገር. ጠብ ሳይል ሲቀር ተስፋ መቁረጥ፤ የመሰላቸትና ለነገሮች ያለን ግምት የመውረድ ስሜት ከተፍ ማልቱ አይቀርም። "የምንለፋው ለምንድን ነው?" ያሰኘናል። "የምኀዘው ጨለማ መቼ ነው የሚነጋው?"....... "የልፋቴን ዋጋ መቼ ነው የማገኘው?" እያላችሁ ከሆነ ፤ ምላሽ የምታገኙበትን አንድ ድንቅ ታሪክ ላካፍላችሁ። እኔ በግሌ የምጠቀምበት ዘዴ ነው። አንድ ነገር ሞክሬ ለማቋረጥ ሳስብ ይህንን ታሪክ መልሼ ለራሴ እነግረዋለው። የቻይና ባምቡ ዛፍ(ቀርከሀ) አስተዳደጉ ከሌሎች ዛፎች በጣም ይለያል። ሌሎች ዛፎች ከተተከሉ ጀምሮ ማቆጥቆጥ ሲጀምሩ፤ ይህ የቻይና ባምቡ ዛፍ ግን፤ በቀን በቀን ውሃ ቢጠጣም እስከ አምስተኛው አመት ድረስ አፈሩን በርቅሶ አይወጣም።ያለማቋረጥ እለት ተእለት ውሃ መጠጣት አለበት፤ ነገር ግን አራት አመት ሙሉ ምንም አይነት እድገት አያሳይም። በአምስተኛው አመት ግን በአምስት ሳምንት ውስጥ በአንዴ 90 ፊት ውይም 27 ሜትር ያድጋል። ታዲያ ይህ ዛፍ በአምስት ሳምንት ውስጥ ነው ያደገው? ወይስ በአምስት አመት? መልሱ በአምስት አመት ነው። ጽናት የሌለው ሰው ግን ቶሎ ብቅ ለማይል ዘር አምስት አመት ሙሉ ውሃ ማጠጣቱ አይዋጥለትም እናም ዛፉን በእንጭጩ ይቀጨዋል። የእኛም ነገር እንዲህ ነው፤ ሃሳባችን ግቡን ባሰብነው ሰዓት ካልመታ፤ አላማችን በአቀድነው ቀን ካለተሳካ፤ ምኞታችን በእለቱ እውን ካልሆነ፤ የማይሳካ ይመስለናል። ለዚህ ነው ብዙዎቻችን ጉዞዋችንን የምናቋርጠው። የእውነት አላማ በውስጥህ ካለ፤ ውሃ ማጠጣትክን እንዳትተው። ዛሬ ባይሳካ በጊዜው መሳካቱ አይቀርም። አንባቢ ባታገኝም መጻህፍህን አትተው፤ የሚጎበኝልህ ብታጣም መሳልህን አትተው፤ የሚሰማህ ብታጣም መዝፈንህን አታቋርጥ፤ አይዞህ የሚልህ ባታገኝ መማርህን አታቁም። የብዙዎቻችን አላማ ልክ እንደ ቻይናው ባምቡ ዛፍ ነው፤ ሳናቋርጥ ውሃ ካጠጣነው እና ትዕግስት ካለን፤ ማቆጥቆጡ ብሎም ማደጉ አይቀርም። ለሁሉም ጊዜ አለው ይል የለ መጽሃፉ.........በጊዜው የተከልነው ችግኝ ሰማይ ማከሉ አይቀርም፤ እስከዛ ግን ማድረግ የሚገባህን ከማድረግ አትቆጠብ፤ ነፍስህ በቀን በቀን ውሃ አጠጣት። የሀገሬ ልጆች ከቻልክ እሩጥ፡ መሮጥ ካልቻክ ተራመድ፡ መራመድ ካልቻልክ ዳህ ፡ መዳህ ካልቻልክ ተንፏቀቅ ብቻ ምንም ይሁን ምን እንቅስቃሴህን እንዳታቆም!!

መልካሙን ተመኙሁ ።

ቸር እንሰንብት!!



# ERMI

## Event Planner and Promoter





**የምንሰጣቸው አገልግሎቶች**

✔የሰርግ
✔የልደት
✔የምርቃት
✔የምስረታ ቀን ሙሉ ዝግጅቶች ማዘጋጀት
✔የገቢ ማሰባሰብያ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት
✔ኮንፈረንሶችንና ሴሚናሮችን ማዘጋጀት
✔የንግድ ድርጅቶችን ማስተዋወቅ
✔አዲስ የተከፈቱ ሆቴሎችን እና ትምህርት ቤቶችን ማስተዋወቅ
✔የትምህርት ቤት በዓላት(Day) ማዘጋጀት።
✔ሾው እና ትርኢት ማዘጋጀት

በአስተማማኝ የኤሌክትሪክ፡የሳወንድ ሲስተም :የሙዚቃ ባንድ እና ዘመኑ ያፈራቸውን የቴክኖሎጂ ውጤቶች በመጠቀም ጥራት ያለው ስራ ባመረ የህትመት እና ዲኮሬሽን፡ ከተሟላ የትራንስፖርት አገልግሎት ጋር በተመጣጣኝ ዋጋ እንሰራለን።

ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ፕሮግራሞች የ30 %ቅናሽ እናደርጋለን።

#አድራሻ -አዲስ አበባ
-መቀሌ

✆0912178520
✆0926721587... ይደውሉ!!


MH
Graphics
Latest Graphics Design
+ Contact Us
0920019699



በ ዞስ ካለስ

# ቴክኖሎጂ

## የ2018 ምርጥ አስር የፈጠራ ገፀ በረከቶች

ዓለም አሁን እየሄደችበት ባለው ፍጥነት አዲስ ነገር መጠበቅ ሳይሆን፣ አዲስ ነገር አለመጠበቅ ይመስላል ግርምት የሚፈጥረው። በእያንዳንዱ ሰዓት፣ ደቂቃና ሰከንዶች ውስጥ ማን ምን እንደሚሰራ፣ ማን ምን ዓይነት የቴክኖሎጂ ውጤቶች እንደሚፈበርክ መገመት ከባድ ነው። ሁሉም አዲስ ፈጠራ አለ። ሁሉም አሮጌ ሚጣል ነገር አለ። ዓለም ባለፈችባቸው በዚህ ጥቂት ሁለት ክፍለ ዘመናት ብቻ፤ የሰው ልጅ ያመጣቸው ለውጦችና ቴክኖሎጂዎች፣ ለብዙ ሺህ ዘመናት የሰው ልጅ ካስመዘገባቸው ፈጠራዎች በብዙ እጥፍ ይበልጣሉ። እነዚህ አዳዲስ ለውጦችና ቴክኖሎጂዎች በትልቅ ግስጋሴ ላይ እንዳሉ ያሳያል። የሚገርመው ነገር ፍጥነታቸው ብቻ ሳይሆን ምን ላይ እንደሚደርሱና እስከ የት ሚለው ነገር የሁሉም ሰው ጥያቄ መሆኑ ነው። አሁን ባለንበት 2019 ገና ሁለተኛው ወር እንኳን በቅጡ ሳናጋምስ አስደናቂ ፈጠራዎችን እያየን ያለንበት ሁኔታ ነው ያለው። ይሁንና በ2018 ብዙ ፈጠራዎች ቢኖሩም ምርጥ 10 ያልናቸውን ፈጠራዎች ለመዳሰስ እንሞክራለን።




### የምንግዜም ፈጣኗ መንኮራኩር

አሜሪካን ሰራሽ ‹‹ፓርከር ሶላር ፕሮብ›› የምትባለው በናሳ ጠቢባን የተፈበረከችው ይህች አስደናቂ መንኮራኩር፤ ባሳለፍነው የፈረንጆች ዓመት ላይ የሁሉም ሰው መነጋገሪያ መሆኗ የሚታወስ ነው። ይበልጥ ነገሩን አጓጊ ያደረገው በከፍተኛ ሙቀት ወደምትታወቀው ፀሐይ ጉዞዋን ማድረጓ ነው። ብዙ እንደተለፋባት የሚነገረው ይህች መንኮራኩር በሰዓት 430,000 ማይል ወይም 692,017.9 ኪሎሜትሮችን መጓዝ ስትችል፤ በፀሐይ ኮሮና(የፀሐይ የውጨኛው ንብብር ከፍል) በሚባለው አካል ላይ ምርምር እንድታደርግ የ7 ዓመት ተልኮ አንግባ ተጉዛለች። ፀሐይን በዚህ ያህል ቅርበት የትኛውም መንኮራኩር ቀርቦ እንዳማያቅም የተነገረ ሲሆን፤ በፀሐይ ሰሜናዊ በኩል ያለውን 2500 ድግሪ ፋራናይት ሙቀት ለመቋቋም አራት ማቀዝቀዣ አካላት የተገጠሙላት ሲሆን፤ እያንዳዳቸው ኔገቲቭ 85 ድግሪ ፋራናይት ቅዛቃዜ አላቸው። ወደ 97% የሚሆነው የመንኮራኩሯ አካል በአየር የተሞላ ሲሆን፤ ይህም ቁሳዊው የመንኮራኩሯ ክፍሎች ለፀሐይ እንዳይጋለጥ ይረዳል ተብሎላታል።



### H160 ኤሊኮፍተር

በኤርባስ የተሰራውና ምርጥ የተባለለት ኤሊኮፍተር አደጋን የማስተናገድ መጠኑ ከሌሎቹ የተሻለ ነው። ለአደጋ ምክኒያት የሆኑ የኃይል መስመሮች፣ አደገኛ ንፋስና ውሽንፍርን በቀላሉ መቋቋም ይችላል። ለአደገኛ ተልዕኮ፣ ለምቹ(VIP) መጓጓዣ በጣም ተመራጭ ሲሆን፤ በፍጥነት እንዲሁም በዝግታ በፈለገው አቅጣጫ መጓዝ ይችላል።ምናልባት አደጋ ቢያጋጥም፤ በመከሰከስ ግዜ ፓይለቱ አደጋ ውስጥ ቢገባ እና እራሱን መቆጣጠር ባይችል እንኳን ከአደጋ ቀጠና ፓይለቱን ተቆጣጥሮ ማስወጣት የሚያስችል ቴክኖሎጂ ተገጥሞለታል። የራሱን ሚዛን በሚገባ መቆጣጠር የሚችለው ይሄ ኤሊኮፍተር፤ በፊት ከተሰሩት ፈጠራዎች ራሱን አሻሽሎ የመጣ ሲሆን ውስጡ በተገጠሙለት አዳዲስ ዲዛይኖች ተመራጭ ሆኗል።



### የጀት ሞተር በሰው አካል ላይ

በምስሉ ላይ የሚታየው ይሄ አስደናቂ ፈጠራ፤ በሰው አካል ላይ የጀት ሞተር በመግጠም፤ ‹‹iron man›› በሚባለው ፊልም እነደሚተውነው ገጸባሀሪ ተቀራራቢ ዲዛይን፤ በሁለት እጅ እና በጀርባ በኩል በተገጠመ የማንቀሳቀሻያ ሞተሮች በአየር ላይ ለ8 ደቂቃ ያህል መብረር የሚያስችል ቴክኖሎጂን እንኩ ብለውናል። ለዚህም እስከ 1000 የፈረስ ጉልበት እንደሚያስፈልገው ተነግሮለታል።



### ፈጣኗ የኤሌክትሪክ መኪና

እጹብ እጹብ የሚያሰኘው የዚች መኪና አሰራር፣ 1914 የፈረስ ጉልበት፣ 258mph ፍጥነት ፣ በ1.9 ሴኮንድ ውስጥ 60mph መፈርጠጧ እና 1700 ጫማ እንደፈለጋት መዞሯ ድንቅ አስብሏታል። ይኼ ሁሉ ግን ዜሮ የአየር ብክለት ባላት ሲ2 ራማክ በምትባለው የስፖርት መኪና ምክንያት ነው። የመኪናዋን አምራቾች ሳይቀር አኩርታቸዋለች።



### አፕል ወች ሲሪየስ 4(Apple watch series 4)

የአፕል ምርት የሆነው ‹‹ስማርት ወች 4›› በሰዓት ዘርፍ ብዙ ድንቅ ፈጠራወችን ይዞልን መቷል። ለምሳሌ የደም-ስር ትርታችንን መጠንና እንዴት መረጋገት እንደምንችል መመሪያ ይሰጣል። የእግር የእርምጃ እንቅስቃሲያችንን መለካት እና ጥርት ያለ ድምፅም ማስተላለፍ ይችላል። ኤሌክትሮ ካርዲዮ ግራም(ECG) መለካት ይችላል። ይሄ ማለት በዶ/ር ቢሮ የሚከናወነውን የልብን ምት እንቅስቃሴ ልኬት ተግባር ‹‹አፕል ወች›› መስራት ይችላል። በዚህም በህክምናው ዘርፍ ትልቅ መነቃቃትን ፈጥሯል። በአሜሪካ ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ተቀባይነትን አግኝቷል። አቅጣጫ መጠቆሚያና ለ18 ሰዓት መቆየት ሚችል ባትሪ በውስጧ ይዛለች።



**ማቪስ 2 ዙም**
በአየር ላይ ያሉ ድሮኖች A+ ካሜራ ከተገጠመላቸው መሬት ላይ ያሉትን ቅጽበታዊ ድርጊቶች ማንሳት አይችሉም ወይም ያመልጣቸዋል። በፈለጉት መጠን፣ ስፋትና ጥልቀት ማስተካከልም እንደዛው አዳጋች ነው። ማቪስ 2 የተባለው አዲሱ ድሮን ግን 2× የተባለ ሌንስ(የእይታ መነጽር) ስላለው፣ በፈለገው አቅጣጫና ርቀት ላይ ሆኖ በአስገራሚ የካሜራ ጥራት ወደ ፈለገው ቦታ ማንሳትና እይታውንም ማስተካከል ይችላል። በአከባቢው ግጭት ሊፈጠር ከሆነና አደጋ ውስጥ የሚገባ ከሆነ፣ ውስጡ ባሉ ሴንሰሮች ራሷን ማዳን ይችላል።
ፈጣኗ የኤሌክትሪክ መኪና
እጹብ እጹብ የሚያሰኘው የዚች መኪና አሰራር፣ 1914 የፈረስ ጉልበት፣ 258mph ፍጥነት ፣ በ1.9 ሴኮንድ ውስጥ 60mph መፈርጠጧ እና 1700 ጫማ እንደፈለጋት መዞሯ ድንቅ አስብሏታል። ይኼ ሁሉ ግን ዜሮ የአየር ብክለት ባላት ሲ2 ራማክ በምትባለው የስፖርት መኪና ምክንያት ነው። የመኪናዋን አምራቾች ሳይቀር አኩርታቸዋለች።



**ኤክስ ቦክስ ማጫወቻ(X box PlayStation)**
በማይክሮሶፍት የተፈበረከው ይሄ ዘርፈ ብዙ የጌም ማጫወቻ፣ ሌሎች ጌሞች ላይ ማይሰሩትን ሁሉንም ጌሞች ማጫወት ይችላል። USB- B ማስተላለፊያ እና 193.5 ሚሊሜትር ኤርፎን ሚመስል ማስተላለፊያ ሲኖረው፤ ይሄም በቀላሉ መድረስና የጌሙን ምቾት ይጨምረዋል። ከሌሎች ጌሞች በተለየም ምርጥ ጥራትና ለአካል ጉደተኞች ታስቦ የተሰራ ሲሆን እጅ ለሌላቸው አካል ጉዳተኞች በእግራቸው መጫወት እንዲችሉና ሰፋ ያለ ሌሎች ለአካል ጉዳተኞች ሚሆን አማራጮችን ይዞ የመጣ ነው።



**BD abseq assay**
ይህ አስገራሚ የቴክኖሎጂ ውጤት ያለምንም ችግር RNA(ሕብለ ባህርይ) እና ፕሮቲን ውስጥ ያሉ በሺህ ሚቀጠሩ እያንዳንዷን የሴል ውስጥ ቅንጣት መተንተን ሚያስችል ፈጠራ ነው። ባላፈው ሰኔ ወር ላይ ለገበያ የዋለው ይሄ የቴክኖሎጂ በህክምነው ዘርፍ አመርቂ ውጤቶችን አሳይቶናል። የካሊፎርኒያ ሳንዲያጎ ተመራማሪና የስነ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ሀላፊ የሆኑት ዶ/ር ዶን ቻንግ እንደሚሉት ይሄን ቴክኖሎጂ በቤተ ሙከራ በመጠቀም አስደናቂ ውጤት እንደሰጣቸው ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። በአንድ ቅንጣት ሴል ውስጥ የለምንም እንከን መለየትም ችለውበታል። ይሄም አሁን ላይ አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ሚገኘውን የካንሰርን ምርመራና ህክምና በብዙ መልኩ እንደሚያቀለው ተገልጻል። በአንድ ምርመራም ሁሉንም በሚያስብል ሁኔታ ብዙ የምርመራ ውጤቶችን ያሳያል።



**አማዞን ጎ(amazon Go)**
አዲሱ አማዞን ያቀረበው የግብይት ምርት አሰራር ለየት ያለና የብዙ ሰው ትኩረት መሳብ የቻለ ነው። ገንዘብ ተቀባይም(casher) ሆነ ምንም አስተናጋጅ የሌለው ሲሆን፤ ደንበኞች ወደ እቃ መግዣው(ሱፐርማርኬት) ሲገቡ QR ኮድ ካርዳቸውን በመጠቀም የአማዞን መተግበሪያ አስዳሰው(አሳውቀው) ይገባሉ፣ ውስጥ ከገቡም በኋላም የፈለጉትን እቃ ወደፈለጉበት ቦታ ማጓጓዝ፣ እቃዎቹን ማየት፣ መመለስ እንዲሁም መውሰድ ይችላሉ። ይህ ሁሉ ሲፈጸም ግን በብዙ ሺህ ሚቆጠሩ ካሜራዎች እና መለያዎች የደንባኛውን ማንኛውንም እንቅስቃሴ መቆጣጠር የሚያስችል ሲስተም ተዘርግቷል። የገዙትንም እቃ ምንነት እንዲሁም ዋጋውን ለይቶ በማወቅ በመስመር ላይ(online) ገንዘብ ይቆርጣል።
እንዲሁም ደንበኞችም እቃቸውን ይዘው ወደ ቤት የሚሄዱበትን ቴክኖሎጂ «አማዞን ጎ» በስራ ላይ አውሎታል። ከዚህ በተጨማሪ የገዢውን ፍላጎትና ዝንባሌ በማወቅ እቃ የሚገኝበትን ቦታ መጠቆሚያ መተግበርያም እንዳለው ተነግሯል። ለግዜው በአሜሪካ ብቻ የተጀመረው ይሄ አስደናቂ ግብይት ሂደት ወደ ሌሎች ሀገሮችም በፍጥነት እንደሚሄድ ይገመታል።



የአማዞን ምርት የሆነችው ይቺ አስደናቂ ስፒከር፣ 8microphone ያላት ሲሆን ይሄም ማንኛውንም ትዕዛዝ ጥርት ባለ መልኩ ለመቀበል ይረዳታል፣ ይሄም ምንፈልገውን ሙዚቃ ለመስማት፣ ለማዘዝና በመሀልም ምንፈልገውን ዜና መስማት ከፈለግን፣ ሙዚቃውን እንድትቀንስልን ትዕዛዝ በመስጠት ዜናውን መስማት ታስችለናለች። ካላንደር ላይ ያለውን ቀኖች በማየትም የወደፊት እቅዶቻችንን መጠየቅ ስትችል፣ ከ50000 በላይ የዘፈን ምርጫዎቻችንን ማስተናገድ አቅም አላት። አቅጣጫ የመጠቆሚያ መተግበሪያ ጨምሮ በስፒከር ውስጥ ምትገኘው አሌክሳ በመባል ምትጠረው ፍላጎታችንን በቶሎ በመረዳት ምንፈልገውን የሙዚቃ ጣዕም መክፈት ትችላለች፣ እሱም ብቻ ሳይሆን አላርም መሙለት ከፈለግን ለአሌክሳ መንገር ብቻ ነው ከኛ ሚጠበቀው፣ ሞልታልን ማስታወስ የሷ ስራ ይሆናል።

# ምስጋና

ከሁሉ በፊት በብዙ ላገዘን እና ለረዳን ፡ ጥበቃውን ፡ ምህረቱንና ቸርነቱን ላበዛልን ፡ በዚህች ቅፅፈት በበዛባት ዓለም እኔ እና እናንተ ግን ዛሬ ላይ በያለንበት ለመገኘታችን ፍቃዱ ለሆነው ሀያሉ እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው ፡ ፡

ቀንዲል ዲጂታል መፅሔትን ስናዘጋጅ ሞራል የሰጡንን ያበረታቱንን ፓ/ር ገላና ጥጉ ፡ ምስጋናው ግሸን ፡ ፀጋአብ ወልዱ ምስጋናችን በያሉበት ይድረሳቸው ። እንዲሁም መፅሔታችንን በተወዳጅ የቴሌግራም ቻናላቸው ላይ የለቀቁልንን TIKUAH-ETH እና BOOK FOR ALL የፌስቡክ ግሩፕ ምስገናችን ከልብ ነው ፡ ፡ እናንተም ውድ አንባቢዎች የመጀመርያ ስራችን የሆነውን ይሄን መፅሔት ስላነበባችሁ እና ለምትሰጡን ገንቢ አስተያየት አስቀድመን እናመሰግናለን!!

---------ሰላማችሁ ይብዛ--------

ቀንዲል

Amharic Digital Magazine

@KendilM

ይፈልጉን
@KendilM

ቀንዲል
Amharic Digital Magazine
@KendilM

---------አስተያየት--------
0912178520
0920019699